# የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል

# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# የተማሪ መጽሐፍ

# 4ኛ ክፍል

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# የተማሪ መጽሐፍ

# 4ኛ ክፍል

አዘጋጆች፡-

1.አየለ መሎሬ (M.A)

2. መስከረም አበራ (M.A)

3. ሰናይት ኃ/ሚካኤል (B.A)

አርታኢ፡- እስከዳር ገበያው (ኤም.ኤ)

የጥራት ተቆጣጣሪ ፡-

1. እንግዳ ዘውዴ (ዶ/ር)
2. አወቀ ፀጋዬ (ኤም.ኤ)

የማጣሪያ ንባብ ፡- ምስራቅ ጠና (ዶ/ር)

ጥቅምት 2014 ዓ.ም

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ሲሆን የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ እና የዲላ ትምህርት የቴክኒክ ድጋፍ በ____አማርኛ____ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል፡፡

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2014 ዓ.ም የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስተርና የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ናቸው፡፡

ውድ ተማሪዎች!

## ለዚህ መማሪያ መጽሐፍ ተገቢውን እንክብካቤና ጥበቃ አድረጉ!

ይህ መማሪያ መጽሓፍ የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ነው። መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ።

1.መጽሓፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክ ወይም በወረቀት ሸፍኑት።

2. መጽሓፉን ሁል ጊዜ በደረቅና በንጹህ ቦታ አስቀምጡት።

3. መጽሓፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ።

4. በመጽሓፉ ሽፋን ወይም በውስጥ ገጾቹ ላይ አትጻፉ።

5. በመጽሓፉ ገጾች መካከል በቦታው ምልክት ለማድረግ ስትፈልጉ ብጣሽ ወረቀት፣ ክር ወይም ካርድ ተጠቀሙ።

6. በመጽሓፉ ውስጥ ያሉትን ሥዕሎች ወይም ገጾች በፉጹም አትቅደዱ።

7. በመጽሓፉ ውስጥ የተቀደዱ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ አጣብቁት።

8. መጽሓፉን ከቦርሳችሁ ውስጥ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ።

9. መጽሓፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ።

10. መጽሓፉን ስትጠቀሙ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጠሉ መጽሓፉን በጀርባው አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)።

<u>ማሳሰቢያ ለመምህሩ፡-</u> በተማሪ መጽሐፉ ከቀረቡ ምንባቦች አብዛኞቹ ተማሪዎች በለሆሳስ እንዲያነቡ የሚያዙ ናቸው። ክፍልዎት ውስጥ ማየት የማይችል ተማሪ ካለ አንብቦ በሚያግዝ ረዳቱ አማካይነት ቀድሞ አንብቦ እንዲመጣ በቤት ስራ መልክ ይስጧቸው። ረዳት የሌለው ከሆነ ክፍል ከመግባትዎ በፊት ከትምህርት ሰኣት ውጪ በማንበብ ያግዟቸው።

# መግቢያ

ይህ የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪ መጽሐፍ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የአማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡

ለዝግጅቱ መነሻ የሆነው አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጀው መርሃ ትምህርት ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች ማዳመጥ፣ መናገር ፣ማንበብና መጻፍ እንዴት እንደሚማሩ መለማመድ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ተማሪዎቹ በደረጃቸው የተለያዩ ባህላዊ፣ ዘመናዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ ፣ኢኮኖሚያዊ፣ አለም አቀፋዊ... ጉዳዮችን በአማርኛ ቋንቋ እንዲገልጹ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የቋንቋ ትምህርት አላማውን ለማሳካት እሴቶቹ እንደ መሳሪያነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ተማሪዎቹ አዳዲስ ጉዳዮችን ለመማር ግላዊ ገጠመኞቻቸውንና ልምምዶቻቸውን ይጠቀማሉ፡፡ በዚህም መሠረት ተማሪዎቹ ቋንቋውን በተለያየ መንገድ እንዲጠቀሙ የሚያስችሉ ችግር ፈቺና አሳታፊ ተግባራት እንዲሁም መልመጃዎች በየምዕራፎቹ ተካተዋል፡፡ በመሆኑም፡-

.ተማሪዎች ሥዕሎችን በመመልከት፤ ተረቶችን ወይም ታሪኮችን በማዳመጥ፤ የማዳመጥና የመናገር ክሂላቸውን ያዳብራሉ፡፡ የሚነበብላቸውን ታሪክ ወይም ምንባብ በማዳመጥ ያዳመጡትን ታሪክ ወይም ምንባብ በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ይገልጻሉ፡፡ ይህንንም ለማድረግ ይችሉ ዘንድ ተከታታይ የመናገርና የመጻፍ ተደጋጋሚ ልምምድ ማድረግ አለባቸው፡፡ በተለመዱና በአዳዲስ ቃላት የተመሠረቱ አረፍተ ነገሮችን ያነባሉ፡፡ ተማሪዎቹ አዳዲስ ቃላትን ሲያዳምጡና ሲያነቡ የአዳዲስ ቃላትን ፍች አብረው መማር አለባቸው፡፡ በዚህም የሚያዳምጡትንና የሚያነቡትን ሀሳብ ይረዳሉ፡፡ የቃላት ዕውቀታቸውንም በማሳደግ በንግግርና በጽሁፍ ሀሳባቸውን በአግባቡ ይገልጻሉ፡፡

.የተለያዩ ተረቶችንና ሌሎች ጽሁፎችን አንብበው መረዳት ይችሉ ዘንድ የአንብቦ መረዳት ተግባራትን በተደጋጋሚ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ መማሪያ መጽሀፍም ተማሪዎች ከላይ የተጠቀሱ አላማዎችን ከግብ እንዲያደርሱ በመሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡

# ማውጫ


ምዕራፍ አንድ ....................................................................................1
የቤትና የዱር እንስሳት..............................................................................1
ምዕራፍ ሁለት ..................................................................................17
ባህላዊና ዘመናዊ አልባሳት ...................................................................17
ምዕራፍ ሦስት ..................................................................................33
የቤት ውስጥ መገልገያዎች........................................................................37
ምዕራፍ አራት ..................................................................................41
የንጽህና አጠባበቅ ..................................................................................41
ምዕራፍ 5 ............................................................................................54
መጓጓዣ ...............................................................................................54
ምዕራፍ ስድስት ..................................................................................67
የምግብ አይነትና አዘገጃጀት ....................................................................67
ምዕራፍ ሰባት ....................................................................................76
የሙዚቃ መሳሪያዎች .............................................................................76
ምዕራፍ 8 ............................................................................................91
ባህላዊና ዘመናዊ ጨዋታዎች...................................................................91
ምዕራፍ ዘጠኝ......................................................................................103
አካባቢያችን.........................................................................................103
ምዕራፍ አሥር.....................................................................................116
ተረት ..................................................................................................116
ዋቢ መጻሕፍት ....................................................................................122

# ምዕራፍ አንድ

# የቤትና የዱር እንስሳት

**አጠቃላይ ዓላማ ፡-**

**ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- **የተለያዩ የቤትና የዱር እንስሳት ስሞችን ትዘረዝራላችሁ፡፡**
- **እንስሳቱ እራሳቸውን ከጠላቶቻቸው የሚከላከሉባቸውን መንገዶች ትናገራላችሁ፡፡**

**-እንስሳቱ ለሰው ልጆች የሚሰጡትን ጥቅም ትገልፃላችሁ፡፡**

**- ትዕዛዞችን ተከትላችሁ መልመጃዎችን ትሰራላችሁ፡፡**

- **በተገቢው መልኩ ፊደላትን ታነባላችሁ፡፡**
- **ዲቃላ(ድርብ) ሆሄያትን ታነባላችሁ፤ ትጽፋላችሁ፡፡**
- **በተነባቢ የእጅ ጽሁፍ ቃላትና አጫጭር አረፍተ ነገሮችን መስመር ጠብቃችሁ ትጽፋላችሁ፡፡**
- **ከሠጠረዥ ውስጥ በሆሄያት ቃላትን ትመሰርታላችሁ፡፡**

## ትምህርት አንድ፡- አዳምጦ መናገር

## የቤትና የዱር እንስሳት ስሞችን አዳምጦ መናገር

**ተግባራት፡-** ሀ/ ከቤት እንስሳት የምትወዱትን እንስሳ ስም ጥሩ፡፡

ለ/ የዱርና የቤት እንስሳት ልዩነታቸው ምንድን ነው? ተናገሩ፡፡

ሐ/ የቤትና የዱር እንስሳትን ጥቅም ዘርዝሩ፡፡

ከታች የቀረቡትን ምስሎች በመመልከት የእንስሳቱን መጠሪያ ወይም ስም ተናገሩ።

ምሳሌ፡- ተራ ቁጥር 3 አውራ ዶሮ



1



2



3




4



5



6



7



8

## መልመጃ አንድ

**ከላይ የቀረቡ ምስሎችን በመመልከት በእያንዳንዱ ትዕዛዝ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

**ምሳሌ** ፡- 1. በተራ ቁጥር ስምንት የቀረበው እንስሳ ጠላቱን የሚከላከለው ሰውነቱ ላይ ባለው እሾህ ነው፡፡

ሀ/ በተራ ቁጥር 4 የቀረበው እንስሳ ጠላቱን የሚከላከለው ምን በማድረግ ነው?

ለ/ ከላይ የቀረቡትን ምስሎች ተመልክታችሁ የቤትና የዱር እንስሳትን ለይታችሁ ተናገሩ፡፡

ሐ/ በተራ ቁጥር 2 የተጠቀሰውን እንስሳ ተመልክታችሁ ስለ እንስሳው አጠር ያለ ሀሳብ ስጡ፡፡

## ትምህርት ሁለት፡- መናገር

## ምስሎችን ተመልክቶ ጠላቶቻቸውን የሚከላከሉበትን መንገድ መግለጽ


**ተግባራት፡-** ሀ/ በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን እንስሳት ስም በመጥራት ጠላታቸውን የሚከላከሉበትን መንገድ ተናገሩ፡፡


ለ/ በአካባቢያችሁ ያሉ መርዝ አመንጪ እንስሳት ስም ተናገሩ፡፡

**መልመጃ አንድ፡-**


የሚከተሉት እንስሳት ጠላቶቻቸውን የሚከላከሉበትን ዘዴ ተናገሩ፡፡

ምሳሌ፡- ተራ ቁጥር 2 በመናከስ






1 2





3. 4.



5

**ማስታወሻ**

እንስሳት የቤትና የዱር በመባል በሁለት ይመደባሉ፡፡ የቤት እንስሳት የምንላቸው በባህሪያቸው ከሰው ጋር ተላምደው የሚኖሩና የተለያየ ጥቅም የሚሰጡ ሲሆን ለጭነት አገልግሎት፣ ለቤት ጥበቃና ሥጋቸው ለምግብነት የሚውሉ ናቸው፡፡ የዱር እንስሳት የምንላቸው ደግሞ ከባህሪያቸው አንፃር ከሰዎች ጋር በቀላሉ ተላምደው አብረው የማይኖሩና በዱር የሚኖሩ ናቸው፡፡ ጥቅማቸውም ለቱሪስት መስህብነት፣ አንዳንዶቹም ለምግብነት ይውላሉ፡፡ ቆዳቸው ለጫማ መስሪያነት የሚያገለግልም አሉ፡፡ ጠላቶቻቸውንም በመናከስ፣ መርዝ በመርጨት፣ በመራገጥና በመሳሰሉት ይከላከላሉ፡፡

## ትምህርት ሶስት፡- የአማርኛ ቋንቋ ዲቃላ (ድርብ) ሆሄያት

**ተግባራት፡-** ሀ/ ቀደም ሲል የምታውቋቸውን የአማርኛ ሆሄያት ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ለ/ ሲ፣ ስ፣ በ፣ ቤ፣ ቆ፣ ቋ፣ ሚ እና ም በሚሉ ሆሄያት ቃላት መስርታችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

### መልመጃ አንድ

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች በትዕዛዛቸው መሠረት ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡**

1. ኳ፣ ሟ፣ ቧ፣ ቋ፣ ጧ የሚባሉ ዲቃላ ሆሄያትን ለጓደኞቻችሁ እየጠራችሁ አሰሙ፡፡
2. ኳ፣ሟ፣ቧ፣ቋ፣ጧ በእነዚህ ዲቃላ ሆሄያት ቃላትን መስርቱ፡፡
3. ቋንቋ፣ ቧንቧ፣ ቋንጣ፣ ኳደኛ የሚሉ ቃላትን መምህራችሁ ሲጠሩ በማዳመጥ ደግማችሁ ተናገሩ፡፡
4. የሰው ልጅ እርስ በእርሱ የሚግባባው በምንድን ነው?

# ትምህርት አራት፡- ማንበብ

## የእንስሳትን ስም ማንበብ

**ተግባራት፡-** በቤታችሁና በአካባቢያችሁ የሚገኙ የቤትና የዱር እንስሳትን ስም ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## መልመጃ አንድ

ከታች የቀረቡትን ስሞች የቤት እንስሳ ወይም የዱር እንስሳ በሚል ለይታችሁ ከጻፋችሁ በኋላ በንባብ አሰሙ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ድመት | ጉማሬ | ኤሊ |
| አንበሳ | ፈረስ | ፈረስ |
| አውራ ዶሮ | ጃርት | ዝንጀሮ |
| ነብር | አዞ | ሚዳቆ |
| ቀጭኔ | ጅብ | ላም |

## መልመጃ ሁለት

ሀ. የሚከተሉትን አጫጭር አረፍተ ነገሮች ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ በየተራ አንብቡ፡፡

- ከእንቅልፏ ተነሳች፡፡
- ጧፍ አብራልኝ፡፡
- ፏፏቴውን አየሁት፡፡
- ልጇን ትወዳለች፡፡
- ፀጉሯን አበጠረች፡፡
- ቀሚሷን አጠበች፡፡
- ወንድሟን ተሰናበተች፡፡
- ቻው ቻው ብላ ተጓዘች፡፡
- ቋንጣ ይወዳል፡፡
- ቧንቧው ተሰበረ፡፡
- ልጅቷ መጣች፡፡

ለ. ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሆሄያት ከፍ ሲል ከቀረቡት አጫጭር አረፍተ ነገሮች የተወሰዱ ናቸው፡፡ የእያንዳንዳቸውን ሆሄ ስም ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሏ | ሟ | ሯ | ሷ | ቋ | ቧ |
| ፏ | ቷ | ጓ | ጇ | ጧ | |

## መልመጃ ሶስት

የሚከተሉትን ቃላት ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ አንብቡና ትርጉማቸውን ለመምህራችሁ አሳዩ።

| | | |
|---|---|---|
| ጓጎለ | ተቧደነ | መጓተት |
| ሟሸሸ | አጓራ | ተንፏቀቀ |
| ተሯሯጠ | ፏፏቴ | |
| ጧፍ | ቋት | |

# ትምህርት አምስት፡- አረፍተ ነገር መስርቶ ማንበብ

## መልመጃ አንድ

በሚከተሉት ቃላት አረፍተ ነገሮችን ስሩና ድምፃችሁን ከፍ በማድረግ አንብቧቸው።

ምሳሌ፡- 1/ ግመል ሻኛ አለው።

2/ ጅብ ይናከሳል።

| | | |
|---|---|---|
| ግመል | እባብ | ነብር |
| ላም | ጅብ | ሚዳቋ |
| ዝሆን | በሬ | አንበሳ |
| አዞ | ጥጃ | ጥንቸል |

## ትምህርት ስድስት፡- ምንባብ

**ተግባራት፡-** የከረጢት ወርቅ የተሰረቀበት ሰው የሚለውን ምንባብ ከማጠናቀቃችሁ በፊት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

ሀ)ስርቆት ጥሩ ነው ወይስ መጥፎ ነው? ለምን?

ለ) አንድ ሰው ሰርቆ ቢያዝ በአካባቢያችሁ ምን ይደረጋል?

### የከረጢት ወርቅ የተሰረቀበት ሰው

አንድ ባለ ጠጋ አንድ ከረጢት ወርቅ ከቤቱ ተሰረቀበት፡፡ እሱም ወደ ዳኛ ሄዶ ነገሩን ሁሉ ነገረ፡፡ ዳኛውም ከቤት የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ሰብስበህ አምጣልኝ አለው፡፡ ባለ ጠጋውም በቤቱ የሚኖሩ ሰዎችን ሰብስቦ አመጣ፡፡ ዳኛውም ብትር አስመጥቶ ሁሉንም እኩል ቆረጣቸው፡፡ ከዛም ለእያንዳንዱ ሰው አንዳንድ ብትር ሰጠና ብትሩ እናንተ ጋር ያድራል ይሁን እንጂ ወርቁን የሰረቀው ሰው ብትር በአንድ ክንድ ይቀንሳል ብሎ ተናገረ፡፡ ሌባው ይህንን በሰማ ጊዜ ከበትሩ አንድ ክንድ ቆረጠለት፡፡ በማግስቱም በተቀጠሩበት ሰአት ሲመጡ የተሰጣቸውን ብትር እንዲሰበስቡ ታዘዙ፡፡ ከዚያም የሌባው ብትር አጥሮ ተገኘ፡፡ ዳኛው ሌባውን በቀላሉ ያዙት፡፡

(ህሩይ ወ/ስላሴ 1963-1925) ለንባብ እንዲመች ተሻሽሎ የቀረበ

**መልመጃ አንድ**

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልስ ስጡ፡፡


1. በተረቱ ውስጥ የሚነጋገሩት ሰዎች ማንና ማን ናቸው ?
2. የወርቁ ባለቤት (ባለጠጋው) ሌባውን ለማግኘት ወደማን ነው የሄደው?
3. ከወርቁ ባለቤት (ከባለጠጋው) ቤት ውስጥ ብትሩ ያጠረው የማን ነው?
4. የተረቱን መልዕክት (ሀሳብ ) ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
5. ዳኛው ለባለጠጋው ምን ትዕዛዝ ሰጠ?
6. ከተረቱ ምን ጠቃሚ ነገር አገኛችሁ? በክፍል ውስጥ ተወያዩ፡፡
7. እናንተ ባለጠጋውን ሰው ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

## ትምህርት ሰባት፡- የእንስሳትን ምድቦች ማንበብ


**ተግባራት፡- ሀ/ለሰው ልጅ ወተት የሚሰጡ እንስሳት የትኞቹ እንደሆኑ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡**

**ለ/ እንስሳቱን በየምድባቸው ለይታችሁ አንብቡ፡፡**

### ወተት ከሚያመነጩ እንስሳት ውስጥ የሚመደቡት



**ስዕል 1. ላም**



**ስዕል 2.ፍየል**



ስዕል 3. ግመል



ስዕል 4. በግ

## ጠላታቸውን በመናከስ ከሚከላከሉ እንስሳት የሚመደቡ



ስዕል 1. ውሻ



ስዕል 2.ቀበሮ




ስዕል 3. ጅብ



ስዕል 4. አንበሳ

## ጠላታቸውን በቀንዳቸው ከሚከላከሉ እንስሳት የሚመደቡ

| | |
|---|---|
|  |  |
| ስዕል 1. ጎሽ | ስዕል 2. ዋሊያ |
|  |  |
| ስዕል 3. አውራሪስ | ስዕል 4. በሬ |
|  | |
| ስዕል 5. አጋዘን | |

**መልመጃ አንድ**

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

ሀ/ ከላይ ከቀረበው ሥዕል ውጭ ወተት አመንጪ እንስሳትን ስም በቡድን ተወያይታችሁ ጻፉና ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

ለ/ በአካባቢያችሁ ለሰው ልጅ የእርሻ አገልግሎት የሚሰጡ እንስሳት አሉ? ካሉ የትኞቹ ናቸው?

ሐ/ የውሻ ጥቅም ምንድን ነው?

**ትምህርት ስምንት፡- አጫጭር ዓረፍተ ነገሮችን መመስረትና ማንበብ**

**መልመጃ አንድ**

የሚከተሉትን ቃላት ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ሰርታችሁ አንብቡ፡፡

**ምሳሌ፡-** የበግ ሥጋ ይበላል፡፡

1.ላም 4.በቅሎ

2.አህያ 5.ፈረስ

3.ፍየል 6.በሬ

**ማስታወሻ፡-** አጫጭር አረፍተ ነገሮች አብዛኛውን ጊዜ ከሁለት ወይም ከሶስት ባልበለጡ ቃላት የሚዋቀሩ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- አየለ መጣ፡፡

ዳንቺሌ ምሳ በላች፡፡

**ተግባር፡- ከዚህ በታች የቀረቡትን አጫጭር አረፍተ ነገሮች አንብቡ፡፡**

ሀ/ እባብ መርዘኛ ነው፡፡

ወተት ከላም ይገኛል፡፡

ከበግ ጸጉር ብርድልብስ ይሰራል፡፡

ከአዞ ቆዳ ቦርሳ ይሰራል፡፡

ከበሬ ቀንድ ማንኪያ ይሰራል፡፡

ከበሬ ቆዳ ጫማ ይሰራል፡፡

## መፃፍ

### ትምህርት ዘጠኝ፡- የእንስሳትን ስም መፃፍ

**ተግባር፡-** የምታውቋቸውን የቤትና የዱር እንስሳት ስሞች በዝርዝር ጻፉ፡፡

**መልመጃ አንድ**

ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላት ከቤትና ከዱር እንስሳት ውጤቶች ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ናቸው፡፡ ቃላቱን ተጠቅማችሁ አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡

**ምሳሌ፡-** አፋይሴ ወተት ጠጣች፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ቀበቶ | አይብ | አልጋ |
| ቦርሳ | ጃኬት | ወተት |
| ዋንጫ | ጫማ | ማንኪያ |
| ቅቤ | መቀመጫ | |

## መልመጃ ሁለት

ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት እንስሳት ስሞች እየመረጣችሁ ክፍት ቦታዎችን አሟሉ። ከአንድ በላይ መልስ መፃፍ ይፈቀዳል።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጅብ | በሬ | ውሻ | አውራ ዶሮ |
| አዞ | ቀጭኔ | ቀበሮ | ላም |
| ጦጣ | ዝንጀሮ | ድመት | ፍየል |

ምሳሌ ፡- ለእርሻ አገልግሎት የሚውል የቤት እንስሳ በሬ ይባላል።

1.ለሴቶች ቦርሳ መስሪያ የሚያገለግል ቆዳ የሚያስገኘው የዱር እንስሳ --------

ይባላል።

2.ልጇን አዝላ ከዛፍ ወደ ዛፍ የምትዘል እንስሳ ---------------ትባላለች።

3.አይጦችን አድና የምትበላ የቤት እንስሳ -------------ትባላለች።

4.ሌሊት ሌሊት ከፍተኛ ድምጽ የሚያሰማ የዱር እንስሳ ---------------ይባላል።

5.ሲነጋ ሲል የሚጮህ የቤት እንስሳ ------------ይባላል።

# ትምህርት አስር፡- ቃላትን ማዛመድ

## መልመጃ አንድ

በ "ሀ" ስር የተዘረዘሩትን እንስሳት ከ "ለ" ስር በባህሪና በሚሰጡት አገልግሎት ተመሳሳይ የሆነውን ክፍል አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1/ እባብ | ሀ/ የበረሃ እንስሳ |
| 2/ ግመል | ለ/ ለእርሻ አገልግሎት የሚሰጥ |
| 3/ ውሻ | ሐ/ ተናዳፊ እንስሳ |
| 4/ በሬ | መ/ ቤት የሚጠብቅ እንስሳ |

## የአዕምሮ ማበልፀጊያ ተግባራት

ሀ/ ያልተሟሉ ቃላትን በዲቃላ (ድርብ) ሆሄያት አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- አ ------ ረጠ አቋረጠ

1. ---------ሮ
2. --------ንጣ
3. ተ--------ተተ
4. አ------ጉል
5. --------ዳኛ

ለ) የሚከተሉት የቤትና የዱር እንስሳት ለሰው ልጆች የሚሰጡትን ጥቅም ጻፉ፡፡ (ከአንድ በላይ መልስ መስጠት ይቻላል)፡፡

ለምሳሌ፡- ውሻ ቤትን ከሌባ ይጠብቃል፡፡

ሀ/ ላም

ለ/ በሬ

ሐ/ በግ

መ/ ግመል

ሠ/ አዞ

ረ/ ድመት

ሰ/ አንበሳ

ሐ) የሚከተለውን የሠንጠረዥ ጨወታ በመጠቀም ቃላትን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ሀገር

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሚ | ቾ | ረ | ብ |
| ስ | | ጎ | ግ |
| ኳ | ል | ጊ | ፊ |
| ል | | ታ | ሮ |
| ይ | ብ | ን | ብ |
| ሀ | ገ | ር | |

# ምዕራፍ ሁለት

# ባህላዊና ዘመናዊ አልባሳት

**የሚጠበቁ ውጤቶች:-**

**ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- ባህላዊና ዘመናዊ የልብስ አይነቶችን ለይታችሁ ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የለበሳችሁት ልብስ ከምን እንደተሠራ ትናገራላችሁ፡፡
- የለበሳችሁትን የልብስ ቀለም አይነት ለይታችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- የልብስ አይነቶችን ከስያሜያቸው ጋር ታዛምዳላችሁ፡፡
- የአልባሳቱን ስያሜ ተጠቅማችሁ አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ትጽፋላችሁ፡፡
- የልብሶችን ቀለም በመመልከት አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ትጽፋላችሁ፡፡
- የልብስ አይነቶቹ ከምን እንደተሰሩ ይናገራሉ፡፡
- ቃላትና አረፍተ ነገሮችን በተገቢው መልኩ ታነባላችሁ፡፡
- ምንባቡን መሰረት አድርጋችሁ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡
- በተውላጠ ስሞች አረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡

## ትምህርት አንድ፡- አዳምጦ መናገር

### የልብሶችን ስያሜ መናገር

ተግባራት ፡-ሀ. የለበሳችኋቸውን ልብሶች ስም ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. ጠባብ ወይስ ሰፊ ልብስ መልበስ ትወዳላችሁ? ለምን?

ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**መልመጃ አንድ**

**የቀረቡትን ምስሎች በመመልከት የልብሶችን ስም ተናገሩ፡፡**

**ምሳሌ ፡- ተራ ቁጥር 5. ጋቢ**




**ስዕል 1**



**ስዕል 2**



**ስዕል 3**



ስዕል 4



ስዕል 5



ስዕል 6

## መልመጃ ሁለት

ከላይ የቀረቡትን ምስሎች በማየት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ለ. ከጥጥ የተሰራ ጋቢ

| |
|---|
| ሀ. ተራ ቁጥር 4 ላይ የቀረበው ልብስ ከምን እንደተሠራ ተናገሩ፡፡ |
| ለ. በተራ ቁጥር 2 ላይ የቀረበው ቀሚስ ከምን እንደተሠራ ተናገሩ፡፡ |
| ሐ. ተራ ቁጥር 1 ላይ የቀረበው ልብስ ምን ይባላል? |
| መ. ተራ ቁጥር 6 ላይ የቀረበው የልብስ አይነት ከምን እንደተሠራ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡ |

**ተግባር፡- መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ የሚያነቡላችሁን የልብስ ስሞች አዳምጣችሁ ልብሶቹ ከምን እንደተሠሩ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።**

## ትምህርት ሁለት፡- ስዕሉን በማየት የልብሱን አይነት መግለፅ

**ተግባራት ፡-** ሀ. አብዛኛውን ጊዜ የምትለብሱት ልብስ ቀለሙ ምን አይነት ነው? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ለ. የለበሳችሁት ልብስ መጠኑ ረጅም ወይም አጭር እንደሆነ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

### መልመጃ አንድ

**የቀረቡትን ምሳሌዎች በማየት የልብሶቹን የቀለም አይነት ተናገሩ።**

ምሳሌ፡- ተራ ቁጥር 3 <u>ሰማያዊ ቀሚስ</u>

| | |
|---|---|
|  |  |
| 1 | 2 |
|  |  |
| 3 | 4 |

| | |
|---|---|
|  |  |
| 5 | 6 |

**መልመጃ ሁለት**

**ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ. ስፖርት ስትሰሩ የምትለብሱት የየራሳችሁ ልብስ ቀለም ምን አይነት እንደሆነ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. እናንተ የለበሳችሁት ቀሚስ፣ ሱሪ፣ ሹራብ ወይስ ሌላ ነው? ቀለሙስ? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ትምህርት ሶስት፡- ምስሎችን አይቶ ልብሶቹ ከምን እንደተሰሩ መናገር

**ተግባራት፡-** ሀ. የለበሳችሁ ልብስ ከምን የተሰራ እንደሆነ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. ከምን የተሰራ ልብስ ትወዳላችሁ? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## መልመጃ አንድ

ልብሶቹ ከምን እንደተሠሩ ተናገሩ፡፡

**ምሳሌ ፡- ተራ ቁጥር 2፣ ከጥጥ የተሰራ ልብስ ነው፡፡**

| | |
|---|---|
|  |  |
| 1. ሌዘር ጃኬት | 2. የሀበሻ |
|  |  |
| 3. በእጅ የተሠራ ሹራብ | 4. ጋቢ |



5.ረዥም ጉርድ

### መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ስዕል በመመልከት በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. በተራ ቁጥር 3 ላይ ያለው ልብስ ከምን የተሠራ ነው?
2. ተራ ቁጥር 1 ላይ ያለው ልብስ የተሰራው ከምንድን ነው?
3. ከቀረቡት ስዕሎች ውስጥ እናንተ የምትወዱት የልብስ አይነት የቱ ነው?
4. በተራ ቁጥር 2 ላይ የቀረበው የልብስ አይነት ከምን የተሠራ ነው?

## ትምህርት አራት፡- አዳምጦ መናገር

### መልመጃ አንድ

መምህራችሁ በመምህሩ መምሪያ የቀረበውን የሐመር ብሔረሰብ ባህላዊ አልባሳትን የተመለከተ ምንባብ ሲያነቡላችሁ በትኩረት አዳምጣችሁ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ሸራን የሚባል ግልድም የሚሰራው ከምንድን ነው?
2. ቃሼ የሚባለው ምንድን ነው?
3. ቶቆ እና ፋላንቲ የተባሉ ስሞች የትኛውን ልብስ ያሳያሉ?
4. የሐመር ሴቶች ከማግባታቸው በፊት የሚለብሱት የልብስ አይነት ምንድን ነው?
5. የሐመር ሴቶች ካገቡ በኋላ የሚለብሱት የልብስ አይነት ምንድን ነው?

## ትምህርት አምስት፡- ባህላዊ አልባሳትን ለይቶ መናገር

### መልመጃ አንድ

ቀጥሎ የቀረቡትን ስዕሎች በመመልከት የየትኛውን ብሔረሰብ ባህላዊ ልብስ እንደሚያመለክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

| | |
|---|---|
|  |  |
| **ስዕል1** | **ስዕል 2** |
|  |  |
| **ስዕል 3** | **ስዕል 4** |

| | |
|---|---|
|  |  |
| **ስዕል 5** | **ስዕል 6** |

|  |  |
|---|---|
| ስዕል 7 | ስዕል 8 |

## ትምህርት ስድስት፡- ማንበብ

### የልብሶችን ስም ማንበብ

**ተግባር፡-** ጓደኞቻችሁ የለበሷቸውን ልብሶች ስም ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

**ትዕዛዝ፡-** ቀጥሎ የቀረቡትን ሐረጎች አንብቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| የሐበሻ ቀሚስ | ጠባብ ሱሪ | የሱፍ ልብስ |
| ሙሉ ልብስ | ወፍራም ሹራብ | አጭር ቁምጣ |
| ቀይ ሸሚዝ | ባህላዊ ልብስ | የክር ሹራብ |
| ወፍራም ጋቢ | ዘመናዊ ልብስ | |

**መልመጃ አንድ**

**በሚከተሉት ሀረጎች አጫጭር አረፍተ ነገሮችን መስርታችሁ ድምጻችሁን ከፍ በማድረግ አንብቧቸው፡፡**

**ምሳሌ፡- ረጅም ቀሚስ አለኝ፡፡**

1. አጭር ቀሚስ
2. ዘመናዊ ልብስ
3. ቢጫ ሽሚዝ
4. ሰማያዊ ቁምጣ
5. ረጅም ሱሪ
6. ብርቱካናማ ቀሚስ
7. ረጅም ቀሚስ

## ትምህርት ሰባት፡- አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ማንበብ

**ትዕዛዝ፡- ከዚህ በታች የቀረቡትን አጫጭር አረፍተ ነገሮች በትክክል አንብቧቸው፡፡**

- ካፖርት ከብርድ ይከላከላል፡፡
- ወፍራም ጃኬት በክረምት ይለበሳል፡፡
- ከነቴራ በበጋ ይለበሳል፡፡
- ቲሸርት ለበጋ ይጠቅማል፡፡
- ጋቢ ከጥጥ ይሰራል፡፡
- ልብስን በንጽህና መያዝ ያስፈልጋል፡፡
- ካፖርት የእስፖርት ልብስ አይደለም፡፡
- የሀበሻ ቀሚስ በበአል ቀናት ይለበሳል፡፡

**መልመጃ አንድ**

**በምሳሌው መሠረት በሚከተሉት ቃላት አረፍተ ነገሮችን ሥሩና ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

**ምሳሌ፡-** ቁምጣ በስፖርት ክፍለ ጊዜ ከሚለበሱ ልብሶች አንዱ ነው፡፡

ሀ. ቁምጣ
ለ. ሸሚዝ
ሐ. ቱታ
መ. ሹራብ
ሠ.ወፍራም ጃኬት
ረ.ካፖርት
ሰ.የአንገት እስካርፕ

## ትምህርት ስምንት፡- ማንባብ

**ተግባራት፡-**

ሀ. የአራዊት ንጉስ የሚለው የትኛው እንስሳ ነው?

ለ. አውራ ዶሮ የቤት እንስሳ ነው ወይስ የዱር እንስሳ?

ሐ. የሚከተሉትን ቃላት ትርጉማቸውን አስረዱ፡፡

1 ትንኝ 2 ዝሆን 3. ፈጣሪ

**ከዚህ በታች አንበሳ ፈጣሪውን ይቅርታ ጠየቀ የሚል ተረት ቀርቦላችኋል፡፡ ተረቱን ረጋ ብላችሁ አንብባችሁ ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

### አንበሳ ፈጣሪውን ይቅርታ ጠየቀ

አንበሳ ፈጣሪውን እንዲህ ብሎ አማረረ "የአራዊት ሁሉ አለቃ አድረገህ ፈጥረኸኝ እንዴት አውራ ዶሮን እንድፈራ አደረከኝ? ጅብን፣ ዝሆንን፣ ጎሽን የማልፈራ ጀግና እዚህ ግባ የማይባል አውራ ዶሮ መፍራቴን ቢሰማ ፍጥረት ሁሉ ጉድ አይልምን?"

## ጥያቄ ፡- አንበሳ ፈጣሪውን ያማረረው ለምን ይመስላችኃል?

አያ አንበሳ በዚህ አይነት ዘወትር ሲቆጭ ኖሮ አንድ ቀን ወንዝ ሲወርድ ዝሆንን ያገኘዋል፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ዝሆንን ልብ ብሎ ሲመለከተው ካለማቋረጥ ጆሮውን ያርገበግባል፡፡ ታድያ አንበሳ በጣም ተገርሞ “አያ ዝሆን ለመሆኑ ካየሁ ጀምሮ ጆሮህን ያለማቋረጥ የምታርገበግበው ለምንድን ነው?” ሲል ይጠይቀዋል፡፡ አያ ዝሆንም “ይህች ትንሽ ትንኝ ወደ ጆሮዬ ብትገባብኝ ስለምትገድለኝ እርሷን ለመከላከል ነው፡፡” ይለዋል፡፡ አንበሳም ይህንን ሲሰማ አምላኩን ይቅርታ ጠየቀ፡፡ “ጌታዬ ይቅር በለኝ፡፡  ይህን የሚያክል ግዙፍ

እንስሳ ትንኝን የፈራ፣ እኔ አውራ ዶሮን ብፈራ ምን ያስደንቃል፡፡ ለካስ መማረሬ አግባብ አይደለም፡፡”

## መልመጃ አንድ

**ተማሪዎች ከላይ የቀረበውን ተረት አንብባችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች  መልሱ፡፡**

1. የአራዊት ሁሉ አለቃ የተባለው ማን ነው?
2. አንበሳ የተቆጨው በምን ምክንያት ይመስላችኋል?
3. አንበሳ ከዕለታት አንድ ቀን ወንዝ ዳር ያገኘው ማንን ነው?
4. ጆሮውን ያለማቋረጥ ሲያርገበግብ የነበረው እንስሳ ማነው?
5. አንበሳ አምላኩን ይቅርታ የጠየቀው ምን በሰማ ጊዜ ነው ?
6. ተማሪዎች ከዚህ ተረት ምን ተማራችሁ?

**መልመጃ ሁለት**

**ከላይ የቀረበውን ተረት መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

_________ 1. አንበሳ የተናደደው ዶሮን ስለሚፈራ ነው፡፡

_________ 2. በተረቱ ውስጥ እራሱን የአራዊቱ ሁሉ አለቃ አድርጎ የሚያየው ጅብ ነው፡፡

_________ 3. በተረቱ ውስጥ የተነገሩት አንበሳ፣ ጅብና ጎሽ ናቸው፡፡

_________ 4. ዝሆን ያለ ማቋረጥ ጆሮውን የሚያርገበግበው ጆሮ ውስጥ ትንኝ ገብቶ እንዳይገድለው ነው፡፡

**መፃፍ**

## ትምህርት ዘጠኝ፡- የልብስ አይነቶችን ከስያሜያቸው ጋር ማዛመድ

**መልመጃ አንድ**

**በ "ሀ" ስር የቀረቡትን የልብስ አይነቶች እያያችሁ በ "ለ" ስር ከቀረቡት ስያሜያቸው ጋር አዛምዱ፡፡**

| | "ሀ" | "ለ" |
|---|---|---|
| ------ 1. |  | ሀ.ቀይ ቀሚስ |
| ------ 2. |  | ለ. ነጭ ጋዋን |
| ------ 3. |  | ሐ. አረንጓዴ ጃኬት |

| | | |
|---|---|---|
| ------ 4 |  | መ. ቢጫ ቲሸርት |
| ------ 5. |  | |

## መልመጃ ሁለት

ሥዕሉን በማየት ለክፍት ቦታው በምሳሌው መሠረት ትክክለኛውን ስያሜ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ተራ ቁጥር 2 ጋቢ



1. ————————ዘመናዊ ልብስ ነው፡፡



2. ————————————የሽመና ውጤት ነው፡፡



3. ———---------ከቆዳ ውጤት ይሰራል፡፡



4. ----------አብዛኛውን ጊዜ በበአላት ቀን የሚለበስ ነው ፡፡



5. ——————---ከበጋ አልባሳት አንዱ ነው፡፡

## ትምህርት አስር፡- ልብሶች የሚሰሩባቸውን ግብዓቶች አንብቦ መፃፍ

**ተግባራት ፡-** ሀ/ የለበሳችኋቸው ልብሶች ከምን እንደተሰሩ በዝርዝር ፃፉ፡፡

ለ/ ስለ ዘመናዊ ልብስ የምታውቁትን በአጭሩ ጻፉ፡፡

**ማስታወሻ**

ባህላዊም ሆነ ዘመናዊ ልብሶች ከተለያዩ ግብአቶች ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡-

**ከቆዳ የሚሠሩ ልብሶች፡-**
ሌዘር ጃኬቶች፣ ዘመናዊ የሌዘር ጉርዶች፣ የሌዘር ታይት፣ ጫማዎች፣ ቦርሳዎች ወዘተ ናቸው፡፡

**ከጥጥ የሚሠሩ ልብሶች፡-**
የሀበሻ ቀሚስ፣ ጋቢ፣ ብሉኮ፣ ሱሪ፣ ሹራብ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

**ከበግ ጸጉር የሚሰሩ ልብሶች፡-** እንደ ብርድ ልብስ እና በርኖስ ያሉ ልብሶች ይጠቀሳሉ፡፡

**ከሐር፡-** የአንገት ልብስ፣ ሹራብ ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## መልመጃ አንድ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት አድርጋችሁ በደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡**

1. ከጥጥ የተሰሩ አልባሳትን ዘርዝራችሁ ፃፉ፡፡
2. የቆዳ ውጤቶችን ፃፉ፡፡
3. ከበግ ፀጉር የሚሠሩ ልብሶች ምን ምን ናቸው? ዘርዝራችሁ ጻፉ፡፡

## ትምህርት አስራ አንድ፡- ሰዋስው

### በተውላጠ ስሞች አረፍተ ነገር መመስረት

**ተግባራት፡-** ሀ. ተውላጠ ስሞችን ታውቃላችሁ? ዘርዝሩ፡፡

ለ. ስም እና ተውላጠ ስም ልዩነታቸው ምንድን ነው? ግለፁ፡፡

**ማስታወሻ**

ስም የሚባለው የአንድ ሰው ወይም ነገር መጠሪያ ነው፡፡

**ምሳሌ፡-** መሰረት፣ ዳንችሌ፣ አየለ ፣ ወጋሶ ፣ ጫክሶ፣

ኢትዮጵያ ፣ ሀዲያ ፣ ዲላ ፣ኮንሶ ፣ ወዘተ ናቸው፡፡

ተውላጠ ስም የሚባሉት ስምን ተክተው የሚያገለግሉ ሲሆን እነሱም፡- እኔ፣ አንተ፣ አንቺ፣ እሱ፣ እሷ፣ እኛ፣ እናንተ፣ እነሱ የሚባሉ ናቸው፡፡

**ምሳሌ፡-** ትዕግስት------ እሷ

እነ ትዕግስት ----- እነሱ

ተማሪዎች-------እናንተ ወዘተ

### መልመጃ አንድ

በምሳሌው መሠረት በሚከተሉት ተውላጠ ስሞች አረፍተ ነገር ስሩ፡፡

**ምሳሌ ፡-** እኔ አባቴንና እናቴን እወዳቸዋለሁ፡፡

1. አንተ
2. አንቺ
3. እሱ
4. እሷ
5. እናንተ

# ምዕራፍ ሦስት

# የቤት ውስጥ መገልገያዎች

**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ፡-**

- በስዕላዊ መግለጫዎች ተደግፈው የቀረቡትን የቤት ውስጥ መገልገያዎች ስማቸውን አዳምጣችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ከሸክላና ከብረት የሚሰሩ የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ለይታችሁ ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን ስያሜ ተጠቅማችሁ ዓረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ስም ትጽፋላችሁ፡፡
- የእውነት ሀሰት ጥያቄዎችን ትሰራላችሁ፡፡
- በተውላጠ ስሞች አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

## ትምህርት አንድ፡- አዳምጦ መናገር

### የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ስያሜ መናገር

**ተግባራት፡-** ሀ/ በቤታችሁ ውስጥ ያሉ ከሸክላ የተሰሩ ባህላዊ መገልገያ መሣሪያዎችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ/ እቤት ውስጥ የተለመዱ ዘመናዊ መገልገያዎችን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡


ሐ/ በቤታችሁ ለምግብ መስሪያነት የሚያገለግሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን ተመልክታችሁ ስያሜያቸውን ተናገሩ።**














## መልመጃ አንድ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ስዕል በመመልከት በቃል መልሱ።**

1. ለወጥ መስሪያነት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ዘርዝሩ።
2. የእንጀራ ምጣድ ከምን እንደሚሰራ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
3. የሲኒን አገልግሎት ተናገሩ።
4. ሸንኩርትና ስጋ ለመክተፍ የምንጠቀምበት መሳሪያ ምንድን ነው?
5. ለውሃ መያዣነት የምንጠቀማቸውን ቁሳቁሶች ዘርዝሩ።

## መልመጃ ሁለት

**ከላይ የቀረበውን ስዕል በማየት ቁሶቹ የተሰሩበትን ነገር መሰረት ያደረገ አረፍተ ነገር መስርታችሁ ተናገሩ።**

**ምሳሌ፡-** ጀበና ከሸክላ ይሰራል።

# ትምህርት ሁለት፡- የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ጥቅም መናገር

**ተግባራት ፡-**

ሀ/ ከቤት ቁሳቁሶች ውስጥ እቤታችሁ ቡና ለማፍላት የምትጠቀሚቸው ቁሳቁሶች ምን ምን ናቸው? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ለ/ ቆጮ ለማዘጋጀት የሚያገለግሉትን ቁሳቁሶች ዘርዝራችሁ ተናገሩ።

የቤት ቁሳቁሶችን አገልግሎት መናገር

ምሳሌ፡- ሶፋ፣ ለመቀመጫነት ያገለግላል።

ማንኪያ፣ ለመመገቢያነት ያገለግላል።

## ትምህርት ሶስት፡- ማዳመጥ

**ማስታወሻ ፡-**

**ማዳመጥ ከአራቱ የአማርኛ ቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱ ሲሆን መልዕክትን ከምንጩ የምንቀበልበት ክሂል ነው፡፡ በመሆኑም መልዕክትን ከሬዲዮ፣ ከቴሌቭዥን፣ ከሰው እና ከመሳሰሉት የመረጃ ምንጮች የምናገኝበት ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም መልዕክትን ከምንጩ አዳምጦ ለመረዳትና ለመተግበር በትክክል ማድመጥን ይጠይቃል፡፡**

**መልመጃ አንድ**

**ከዚህ ቀጥሎ መምህራችሁ የቤት ቁሳቁስን የተመለከቱ ቃላት ያነቡላችኋል፡፡ ቃላቱን እያዳመጣችሁ አጫጭር አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

**መልመጃ ሁለት**

ተማሪዎች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያዳመጣችሁትን በክፍል ውስጥ በንግግር አቅርቡ፡፡

## ትምህርት አራት፡- ማንበብ

### የቤት ቁሳቁስ ስም ማንበብ

**ተግባር ፡-** ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ምን ምን አይነት የቤት ቁሳቁስ ይገኛሉ? ስማቸውስ?

**ቀጥሎ የቀረቡትን የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ስያሜ አንበቡ፡፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጋን | በርሜል | የዕቃ መደርደሪያ | ሹካ | መክተፊያ |
| ባልዲ | ፍሪጅ | ወንበር | ማማሰያ | ሙቀጫ |
| ቴሌቪዥን | ጠረጴዛ | ምጣድ | ጭልፋ | ሲኒ |
| በርጩማ | ሸክላ ድስት | ብርጭቆ | ሰፌድ | ረከቦት |
| መሶብ | ማሰሮ | ማንኪያ | ቢላዋ | ጀበና |

### መልመጃ አንድ

**ከላይ የቀረቡትን ስያሜዎች በመጠቀም በምሳሌው መሰረት የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች አሟሉ ፡፡**

ምሳሌ፡- ---------------- ውሃ ለማጠራቀም ያገለግላል፡፡

መልሱ፡- **በርሜል፣ ጋን**

1. ሸንኩርት የሚከተፈው በ --------------------- ላይ ነው፡፡
2. ቤት ውስጥ እህል ለመፍጨት የሚያገለግለው ------------ ነው፡፡
3. እህል የሚቀመጠው በ -------------------------- ነው፡፡
4. ገንፎ መብያ እቃ -------------------------- ይባላል፡፡
5. እንጀራ ማስቀመጫ እቃ -------------------- ነው፡፡
6. ሦስት እግር ያለው አንድ ሰው የሚቀመጥበት መቀመጫ -------- ይባላል፡፡

## ትምህርት አምስት፡- መጻፍ

### የቤት ውስጥ መገልገያ መሳሪያዎችን ስም መጻፉ

**ተግባር፡-** ሀ/ ከቤታችሁ የሚገኙ ባህላዊ ቁሳቁሶችን ስም ጻፉ፡፡

ለ/ በቤታችሁ ውስጥ የሚገኙ ዘመናዊ መገልገያ እቃዎችን ስም ዘርዝሩ፡፡

**መልመጃ አንድ**

**የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎችን ስም አንብባችሁ ከታች በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት ስሩ፡፡**

| | |
|---|---|
| ሸክላ ድስት | ወጥ ማቅረቢያ |
| የብረት መጥበሻ | ሳጥን |
| ሙቀጫ | ቅቤ ማጣሪያ |
| ፓስታ ማጥለያ | አልጋ |
| ማሰሮ | የኤሌክትሪክ ምድጃ |
| የብረት ምጣድ | ጉልቻ |

ከላይ የቀረቡትን የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች ስምና እናንተም የምታውቋቸውን ሌሎች የመገልገያ እቃዎችን ስሞች በደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡

## መልመጃ ሁለት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሰረት በጽሑፍ መልሱ፡፡**

ምሳሌ፡- ሻይ አዘጋጅቶ ለመጠጣት የሚያገለግሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች፡-

ጉልቻ፣ ማንቆርቆሪያ፣ ማንኪያ፣ ማጣሪያ፣ የሻይ ብርጭቆ ወዘተ ናቸው፡፡


1. ለቡና ማፍያነት የሚያገለግሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ዘርዝራችሁ ፃፉ፡፡
2. ለምግብ ማብሰያነት የሚያገለግሉ የቤት እቃዎችን ዘርዝሩ፡፡


## መልመጃ ሶስት

**ከዚህ በታች የቀረቡትን የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎችን ስዕሉን ተመልክታችሁ ስማቸውን ጻፉ፡፡**

ሀ/ 

ለ/ 

ሐ/ 

መ/ 

## ትምህርት ስድስት፡- ሰዋስው

### በተውላጠ ስም አረፍተ ነገሮችን መመስረት

**ተግባር ፡-** የሚከተሉትን ተውላጠ ስሞች ተጠቅማችሁ በምሳሌው መሰረት አረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- እኔ ትግል እችላለሁ፡፡

አንቺ ምን ትችያለሽ?

1. እኔ
2. አንተ
3. አንቺ
4. እሱ
5. እኛ
6. እናንተ

# ምዕራፍ አራት

# የንጽህና አጠባበቅ

**የሚጠበቁ ውጤቶች**

**ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- የግል ንጽህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን ስያሜ አዳምጣችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ስለግልና አካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ሲነገር ወይም ሲነበብ አዳምጣችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ስለኮሮና ቫይረስ ምንነት አንብባችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- የግልና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ጠቀሜታዎችን ትናገራላችሁ፡፡
- የግልና አካባቢ ንጽህና አጠባበቅ መንገዶችን ትናገራላችሁ፤ ትጽፋላችሁ፡፡
- ምንባብ አንብባችሁ የአምብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ትሰራላችሁ፡፡
- ከንጽህና ጋር የተያያዙ ቃላትን፣ ሐረጋትንና አረፍተ ነገሮችን ታነባላችሁ፡፡
- ከንጽህና ጋር የተያያዙ ቃላትን ተጠቅማችሁ ቀለል ያለ አረፍተ ነገር ትጽፋላችሁ፡፡

## ትምህርት አንድ፡- አዳምጦ መናገር

### የግል ንጽህና መጠበቂያ መሣሪያዎችን ስያሜ አዳምጦ መናገር

**ተግባራት፡-** ሀ. የግል ንጽህና ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. የግል ንጽህናችንን ለመጠበቅ ምን ምን ነገሮች ያስፈልጉናል?

### መልመጃ አንድ

ቀጥሎ የቀረቡትን ምስሎች በመመልከት የንጽህና መጠበቂያ መሣሪያ አይነቶቹን ተናገሩ።














**መልመጃ ሁለት**

**ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ስያሜዎች ከአነበባችሁ በኋላ ለጓደኞቻችሁ በቃላችሁ ተናገሩ።**

- የግል ንጽህና መጠበቂያ መሣሪያዎች
  - ✓ ማበጠሪያ
  - ✓ የጥፍር መቁረጫ
  - ✓ የጥርስ ብሩሽ
  - ✓ የጥርስ ሳሙና
  - ✓ የገላ ሳሙና
  - - የልብስ ሳሙና
  - - የውሃ ባልዲ
  - - ብሩሽ
  - - የጥርስ መፋቂያ

- የአካባቢ ንጽህና መጠበቂያ መሣርያዎች
  - ✓ መጥረጊያ
  - ✓ መወልወያ
  - ✓ አካፋ
  - ✓ ቅርጫት

# ትምህርት ሁለት፡- የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ጥቅም

**ተግባር፡-** አካባቢያችሁን እንዴት እንደምታጸዱ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**አቅርቦት፡- የአካባቢ ጽዳት**





## መልመጃ አንድ

**ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ዙርያ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩና የተወያያችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡**

ለምሳሌ፡- የአካባቢ ጽዳት ስንል አካባቢያችን ውብና ማራኪ ገጽታ እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡

1. የአካባቢ ጽዳት ስንል ምን ማለት ነው?
2. አካባቢያችንን ባናፀዳው ምን ምን በሽታዎች ሊይዙን ይችላሉ?
3. የአካባቢ ጽዳት ጥቅም ምንድን ነው?
4. አካባቢያችንን ውብና ጽዱ ለማድረግ ምን አይነት መሣሪያዎች ያስፈልጉናል ዘርዝራችሁ አስረዱ፡፡

# ትምህርት ሶስት፡- የግልና የአካባቢ ንጽህና መጓደል የሚያመጣው ጉዳት

**ተግባራት፡-** ሀ. ተማሪዎች፣ የግል ንጽህናችሁን የምትጠብቁት እንዴት ነው?

ለ. የግል ንጽህናውን የማይጠብቅ ተማሪ ምን አይነት ጉዳት ይደርስበታል? ከጓደኞቻችሁ ጋር እርስ በርስ ተነጋገሩ፡፡

**መልመጃ አንድ**

**መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ስለግልና የአካባቢ ንጽህና የሚያነቡላችሁን ምንባብ አዳምጣችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. የግል ንጽህና ምን ማለት እንደሆነ በዝርዝር አስረዱ፡፡
2. አካባቢያችሁን ውብና ጽዱ ለማድረግ ምን አይነት መሳሪያዎችና ተግባራት ያስፈልጉናል?
3. እራሳችንን ከተላላፊ በሽታዎች ለመከላከል ምን ማድረግ አለብን?
4. የግልና አካባቢ ንጽህና አለመጠበቅ የሚያመጣው ጉዳት ምንድን ነው?

**መልመጃ ሁለት**

**የግልና የአካባቢ ንጽህና መጠበቂያ ሂደት በቅደም ተከተል አዳምጦ መናገር**

**ተግባራት፡-** ሀ. የግል ንጽህና መጠበቂያ ሂደት በቅደም ተከተል ዘርዝራችሁ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. አንድ ሰው የግል ንጽህናውን ባይጠብቅ ምን አይነት ችግር ይፈጠርበታል? ተናገሩ፡፡

**ከዚህ በታች የግልና የአካባቢ ንጽህና መጠበቂያ የተመለከቱ ቃላት ቀርበውላችኋል፡፡ የእያንዳንዱን የንጽህና አጠባበቅ ሂደት ተናገሩ፡፡**

**ምሳሌ፡-** ጥርስን መፋቅ

መፋቂያና ውሃ ማዘጋጀት

ጥርስን በጥንቃቄ መፋቅ

ተጉሞጥሙጦ መትፋት

መፋቂያ አጥቦ ማስቀመጥ

| | |
|---|---|
| ገላን መታጠብ | ጥርስ መፋቅ |
| ቤት ማጽዳት | ጥፍር መቁረጥ |
| ፊታችንን መታጠብ | ቆሻሻ ማስወገድ |
| ጫማችንን ማጽዳት | ልብሳችንን ማጠብ |

## ትምህርት አራት፡- አንብቦ መረዳት

ተግባር፡-ሀ. ስለኮሮና ቫይረስ ምንነትና መተላለፊያ መንገዶች ታውቃላችሁ?

ለ. የኮሮና ቫይረስ መከላከያ መንገዶቹ ምን ምንድን ናቸው? ዘርዝሩ፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የኮረና ቫይረስ ምንነትና የመከላከያ መንገዶቹን የሚገልጽ ጽሁፍ ቀርቦላችኋል፡፡ ምንባቡን አንብባችሁ ጥያቄዎቹን መልሱ፡፡

### ምንባብ አንድ

### ኮሮና ቫይረስ ምንድን ነው?

ኮሮና ቫይረስ በሌላ አጠራር ኮቪድ 19 ተብሎ የሚታወቅ በሽታ ነው፡፡ ኮሮና የአለምን ህዝብ፣ እድሜ፣ ዘር፣ ጾታ፣ ቀለም ሳይለይ ያጠቃል፡፡ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰውም በቫይረስ አማካኝነት ይተላለፋል፡፡ ታህሳስ በ2012 ዓ.ም በቻይና ሁዋን ግዛት ተከስቶ የአለምን ሀያላን አገራት ሳይቀር ያስደነገጠ በሽታ ነው፡፡ በአለም ላይ ብዙ ትምህርት ቤቶችን አስዘግቷል፡፡ የመንግስት መስሪያ ቤቶችም ስራቸውን አቁመዋል፡፡ በጥቂት ወራት ብቻ በብዙ ሚሊየን የሚቆጠረውን የአለም ህዝብ ጨርሷል፡፡ አሜሪካ፣ ጣሊያን፣ ብራዚልና ህንድ በብዙ ሚሊየን የሚቆጠር ህዝብ የሞተባቸው ሀገሮች ናቸው፡፡

በሀገራችንም ብዙ ህዝብ የመታመምና የሞት አደጋ ደርሶበታል፡፡ መንግስት የሀገሩ ህዝብ እንዳያልቅበት አፍና አፍጫቸውን በማክስ እንዲሸፍኑ አዟል፡፡ የናፈቁት ዘመድ ቢመጣ እንኳን እጅ ለእጅ መጨባበጥ ተከልክሏል፡፡ ትኩሳትና

ሳል ካለበት ሰው ከሁለት ሜትር በላይ እንድንርቅ ታወጇል፡፡ በየጊዜውና በየቦታው እጃችንን በውሃና በሳሙና እንድንታጠብ ተደርገናል፡፡ በየጊዜው መልኩን እየቀያየረ አሁን ደግሞ ዴልታ ተብሎ በጣም ፈጣን ገዳይ ሆኖ እየወረረን ነው፡፡ አስተማማኝ መድሃኒት እስከሚገኝ ድረስ የመንግስትን ህጎች አክብረን እራሳችንን ከኮሮና ቫይረስ ልንከላከል ይገባል፡፡

**ምንጭ፡- (ከአዘጋጆች)**

**መልመጃ አንድ**

**ከዚህ በታች በምንባቡ ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. የኮሮና ቫይረስ ምን አይነት በሽታ ነው?
   ሀ.በቫይረስ የሚተላለፍ በሽታ ነው ለ. በባክቴሪያ አማካኝነት የሚመጣ ነው
   ሐ.የብርድ በሽታ ነው መ. የጉንፋን በሽታ ነው
2. ኮሮና የተከሰተው መቼ ነው?
   ሀ.2012ዓ.ም ለ.2014ዓ.ም ሐ.2013ዓ.ም መ.2011 ዓ.ም
3. ኮሮና መጀመሪያ የተገኘው የት ሀገር ነው?
   ሀ. አሜሪካ ለ. ቻይና ሐ. ኢትዮጵያ መ. ጣሊያን
4. ኮሮና እንዳይዘን ምን ማድረግ አለብን?
   ሀ. እጃችንን መታጠብ ለ. እግራችንን መታጠብ
   ሐ. ልብሳችንን ማጠብ መ. ፊታችንን መታጠብ
5. አሁን በጣም ፈጣን ገዳይ የተባለው የበሽታ አይነት የትኛው ነው?
   ሀ. ዴልታ ለ. ወባ
   ሐ. ቁርጠት መ. ታይፎይድ

**መልመጃ ሁለት**

**ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡**

1. ትምህርት ቤቶች የተዘጉት በሽታው ከተማሪ ወደ ተማሪ እንዳይተላለፍ ነው፡፡
2. በበሽታው እንዳንሞት መንግስት አድርጉ ያለንን ማድረግ አለብን፡፡
3. በኮሮና ቫይረስ የሞተው ሰው ብዛቱ አንድ ሚሊዮን ብቻ ነው፡፡
4. በሽታው ከሰው ወደ ሰው በመጨባበጥና በትንፋሽ መተላለፍ ይችላል፡፡
5. በሽታው ልጆችንና ነጮችን አይገልም፡፡

## ትምህርት አምስት፡- ማንበብ

### የግል ንፅህና አጠባበቅ

**ተግባራት፡-** ሀ.የግል ንፅህና ተግባራት ከምን የሚጀምር ይመስላችኋል?

ለ. አንድ ሰው የግል ንፅህናውን ይጠብቃል የሚባለው ምን ሲያደርግ ነው?

## ምንባብ ሁለት

## የግል ንፅህና

**ንፅህና፡-**ንፁህ፣ የጠራ፣ እንከን የሌለውና ጉድለት የሌለበት ማለት ነው። የግል ንፅህና መጠበቅ የፊት፣ የጥርስ፣ የፀጉር፣ የአካላችንንና የልብሳችንን ንፅህና መጠበቅ ማለት ነው።

የሰው ልጅ በህይወት እስካለ ድረስ ለራሱ፣ በአካባቢው ላሉ ሰዎችና ለሚኖርበት ማህበረሰብ ደህንነት ሲል የግል ንህፅናውን መጠበቅ ግድ ይለዋል። የግል ንህፅናችንን ከምንጠብቅባቸው ምክንያቶች ውስጥ በተለያዩ የፅዳት ጉድለቶች ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎችን ለመከላከል ነው። በተጨማሪም ጤናማ የሆነ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እንዲኖረን፤ ከሰዎች ጋር ጤናማ የሆነ አብሮነትን ለመፍጠር እንዲሁም ጤናችን የተስተካከለና በጥሩ አቋም ላይ እንዲገኝ ነው።

ተግባር፡- ከላይ ከቀረበው አንቀጽ ምን ተረዳችሁ?

የግል ንፅህናችንን እንዴት እንጠብቅ? ጠዋት ከመኝታችን እንደተነሳን ፊታችንና እጃችንን በሳሙና በመታጠብ፤ ቁርስ ከመመገባችን በፊት እና ከእራት በኋላ ጥርሳችንን በጥርስ ሳሙና በማፅዳት፤ ጥፍራችን ካደገ የተለያዩ ጀርሞችን ሊይዝ ስለሚችል በመቁረጥ፤ ፀጉራችን በፈንገስ እንዳይጠቃ በየግዜው በመታጠብ፤ ገላችን አላስፈላጊ ጠረን ያለው ላብ እንዳያስተናግድ በየቀኑ በመታጠብ ንህፅናችንን መጠበቅ እንችላለን።

በአጠቃላይ የግል ንህፅናችንን በመጠበቅ የጤና ጠንቅ ከሆኑ ተህዋሲያን እራስን መከላከል ይቻላል። ስለሆነም የግል ንፅህናን መጠበቅ ያለው ፋይዳ ለራስ ብቻ ሳይሆን በዙርያችን ላሉ ሰዎችም ጭምር ነው። ስለዚህም ህይወታችን ዘላቂ የሆነ የጤና ዋስትና እንዲኖረው የግል ንፅህናን መጠበቅ የግድ ይሆናል ማለት ነው።

**(ምንጭ፡- ከአዘጋጆች)**

**መልመጃ አንድ**

**I.የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ በቃል መልሱ፡፡**

1. የግል ንፅህና ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?
2. የግል ንፅህናችንን የምንጠብቅበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. የግል ንፅህናችንን እንዴት እንጠብቅ?
4. የእጃችን ጥፍር ሲያድግ የምንቆርጠው ለምንድን ነው?
5. ተማሪዎች ከዚህ ምንባብ ምን እንደተረዳችሁ? ተናገሩ?

**ማንበብ**

**ትምህርት ስድስት፡- ቃላትን፣ ሀረጋትንና፣ አረፍተ ነገሮችን ማንበብ**

**ተግባራት፡-**

ሀ/ ከንጽህና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ቃላት፣ሀረጎችንና አረፍተ ነገሮችን ተናገሩ፡፡

ምሳሌ፡- መጉመጥመጥ

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት፣ሀረጋትንና አረፍተ ነገሮችን በትክክል አንብቡ።

| የሚነበቡ ቃላትና ሀረጋት | |
|---|---|
| ፊት _______________ | ፊቴን ታጥቤ |
| ልብስ _______________ | ልብሴን አጥቤ |
| እጅ _______________ | እጄን ታጥቤ |
| ገላ _______________ | ገላዬን ታጥቤ |
| ጫማ _______________ | ጫማዬን ወልውዬ |
| ጥፍር _______________ | ጥፍሬን ቆርጬ |
| እግር _______________ | እግሬን ታጥቤ |
| ካልሲ _______________ | ካልሲዬን አጥቤ |
| የውስጥ ልብስ _______________ | የውስጥ ልብሴን አጥቤ |
| ሱሪ _______________ | ሱሪዬን አጥቤ |
| ንጽህና _______________ | ንፅህናዬን ጠብቄ |
| ጥርስ _______________ | ጥርሴን አጽድቼ |

| የሚነበቡ አረፍተ ነገሮች |
|---|
| በረከት ፊቷን ታጠበች። |
| ፋጡማ ልብሷን አጠበች። |
| ነህምያ እጁን ታጠበ። |
| አህመድ ገላውን ታጠበ። |
| እኔ ጫማዬን ወለወልኩኝ። |
| መሰረት ጥፈሯን ቆረጠች። |
| አብዲ እግሩን ታጠበ። |
| ናሆም ከልሲውን አጠበ። |
| የትናየት የውስጥ ልብሷን አጠበች። |
| ከድጃ ሱሪ አጠበች። |
| እኛ ንፅህናችንን እንጠብቃለን። |
| ዘላለም ጥርሱን አፀዳ። |

**መልመጃ:**

**የግንዛቤ ጥያቄዎች:-**

ሀ. ከግል ንፅህና ጋር የተያያዙ ስድስት ቃላትን ፃፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

ለ. ከአካባቢ ንፅህና ጋር የተያያዙ ስድስት ቃላትን ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

ሐ. ስለግልና አካባቢ ንፅህናን መሰረት ያደረገ አስራ ሁለት አረፍተ ነገሮችን ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

## ትምህርት ሰባት:- አዳምጦ መፃፍ

**ተግባራት:-** ሀ.ተማሪዎች ቤተሰቦቻችሁ የግልና የአካባቢ ንጽህና የሚጠብቁበትን መንገድ ጠይቃችሁ ፃፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተመለከተ እንደ ጥያቄዎቹ አካሄድ ተገቢውን ምላሽ በጽሁፍ ስጡ።**

1. አካባቢያችሁ ወዳለው ጤና ጣቢያ በመሄድ ስለግል ንፅህና አጠባበቅና የግል ንፅህናችንን ባለመጠበቃችን ስለሚከሰቱ ችግሮች ጠይቃችሁ ለመምህራችሁ በፅሁፍ አቅርቡ።
2. የአካባቢ ንፅህና መጠበቂያ መንገዶችንና አካባቢያችን ንፁህ ባለመሆኑ ስለሚከሰቱ ችግሮች ጠይቃችሁ በጽሁፍ አቅርቡ።

**መልመጃ ሁለት**

**ከታች ከቀረቡት ቃላት መካከል እየመረጣችሁ ባዶ ቦታዎችን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡**

| ለቆዳ | ለትራኮማ | ፈንገስ | የጥርስ ሳሙና | የላብ ጠረን |
|---|---|---|---|---|

1. _______________የጥርስ ንፅህናን ለመጠበቅ ያገለግላል፡፡
2. የፀጉራችንን ንፅህና መጠበቅ ከ _______________ ይከላከላል፡፡
3. ገላን በሳሙና መታጠብ አላስፈላጊ _______________ ያስወግዳል፡፡
4. የፊትን ንፅህና አለመጠበቅ _______________ በሽታ ያጋልጣል፡፡
5. ገላን በየጊዜው በሳሙና አለመታጠብ ለ _______________በሽታ ያዳርጋል፡፡

## ትምህርት ስምንት፡- ሰዋስው

**በንጽህና ላይ የሚያተኩሩ ተራ አረፍተ ነገሮችን መጻፍ**

**መልመጃ አንድ**

**በንፅህና ላይ የሚያተኩሩ አምስት ተራ አረፍተ ነገሮችን ፃፉ፡፡**

**ምሳሌ፡** - ጠዋትና ማታ ጥርሴን አጸዳለሁ፡፡

ፊቴን ታጥቤ ቁርሴን እበላለሁ፡፡

# ምዕራፍ 5

# መጓጓዣ

**የሚጠበቁ ውጤቶች:-**

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎችን ለይታችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ባህላዊና ዘመናዊ የመጓጓዣ አገልግሎቶችን ታብራራላችሁ፡፡
- የመጓጓዣ ስዕሉን በመመልከት ከስያሜየቸው ጋር ታዛምዳላችሁ፡፡
- ስለ ባህላዊና ዘመናዊ የመጓጓዣ አገልግሎት የቀረቡትን ማስታወሻዎች ታነባላችሁ፡፡
- ቃላትንና አረፍተ ነገሮችን ትፅፋላችሁ፡፡
- ቃላትንና አረፍተ ነገሮችን ታነባላችሁ፡፡
- የመጓጓዣን ጥቅም አስመልክቶ በጭውውት ሀሳብ ትለዋወጣላችሁ፡፡
- የነጠላና የብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስሞችን ትለያላችሁ፡፡

## አዳምጦ መናገር

## ትምህርት አንድ፡- የተለያዩ የመጓጓዣ አይነቶችን መናገር

**ተግባራት፡-** ሀ. በእናንተ አካባቢ የሚገኙ የመጓጓዣ አይነቶችን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. መምህራችሁ የሚነግሯችሁን የመጓጓዣ አይነቶች ባህላዊ እና ዘመናዊ በሚል ለይታችሁ ተናገሩ፡፡

## ማስታወሻ

የመጓጓዣ አይነቶች በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ። እነርሱም፦ የየብስ፣ የባህር፣ የአየር እና የእንስሳት ናቸው።

ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴዎች ፈጣንና ምቹ አስተማማኝ ሲሆኑ ለተጠቃሚው የተቀላጠፈ አገልግሎት ይሰጣሉ። እነሱም በአየር የሚበሩ፣ በየብስ (በምድር) የሚጓዙ እና በውሃ ላይ የሚሄዱ ናቸው።









**መልመጃ አንድ**

**ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ/ ከላይ የቀረቡትን ስዕሎች በመመልከት ዘመናዊ መጓጓዣ የሆኑትን ለይታችሁ ተናገሩ፡፡

ለ/. ከላይ የቀረበውን ምስል በመመልከት የሚጓዙበትን መንገድ ተናገሩ፡፡

ለምሳሌ ፡- መኪና ፡- በየብስ (በመሬት ላይ የሚሄድ ነው፡፡ )

1. ባጃጅ------------------------
2. አውሮፕላን----------------------
3. መርከብ----------------------
4. ብስክሌት---------------------
5. አውቶብስ------------------

## መልመጃ ሁለት

ከላይ የቀረቡትን ስዕሎች በደንብ አስተውላችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ ፡፡

ሀ. በመኪናና በባቡር መካከል ምንም ልዩነት የለም ፡፡

ለ. ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴዎች በሙሉ ባህር ላይ መሄድ አያግዳቸውም፡፡

ሐ. በአውሮፕላንና በመርከብ መካከል ምንም ልዩነት የለም ፡፡

መ. በባጃጅና በአውቶቢስ መካከል የአገልግሎት ልዩነት የለም፡፡


ሠ. ከተጠቀሱት ስዕሎች የቀደመው ባጃጅ ነው ፡፡

## ትምህርት ሁለት፡- ምስሎቹን ተመልክቶ የመጓጓዣ አይነቶችን መግለጽ

**ተግባራት ፡-** ሀ. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ባህላዊ መጓጓዣ አይነቶችን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ ።

ለ. የበረሃ የመጓጓዣ አይነት የሆነውን ለመምህራችሁ ተናገሩ።

**ቀጥሎ የቀረቡትን ስዕሎች ተመልክታችሁ ከታች በቀረበው ትዕዛዝ መሰረት መልመጃዎቹን ስሩ።**

| | |
|---|---|
|  |  |
|  | |
|  |  |

**መልመጃ አንድ**

**ከላይ የቀረበውን ምስል ተመልክታችሁ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡**

1. ከባህላዊ መጓጓዣዎች መካከል በእናንተ አካባቢ አገልግሎት እየሰጡ ያሉትን ዘርዝሩ፡፡
2. ባህላዊና ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴዎችን አወዳድራችሁ ተናገሩ፡፡
3. በአካባቢያችሁ ለባህላዊ መጓጓዣ የሚያገለግሉ እንስሳትን ስም ተናገሩ፡፡
4. ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ የውሃ ጥምን መቋቋም የሚችለው የቱ ነው? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## መልመጃ ሁለት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1.ከሚከተሉት የቤት እንስሳት ውስጥ ለመጓጓዣነት የማያገለግለው የቱ ነው?

ሀ. ግመል　　ሐ. ፍየል

ለ. ፈረስ　　መ. በቅሎ

2.ከሚከተሉት ውስጥ ፈጣኑ መጓጓዣ የቱ ነው?

ሀ. ባጃጅ　　ሐ. መኪና

ለ. አውሮፕላን　　መ. ብስክሌት

3. ቀጥሎ ከቀረቡት ውስጥ በባህር ላይ የሚጓዘው የቱ ነው?

ሀ.መርከብ　　ሐ. ጀልባ

ለ. ታንኳ　　መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4.ባህላዊ የመጓጓዣ ዘዴዎች አድካሚና ዘገምተኛ — እንገለገልባቸዋለን፡፡

ሀ. ስለሆኑ　　ሐ. ቢሆኑም

ለ. መሆናቸው　　መ. ሁሉም

5.ቀጥሎ ከቀረቡት ውስጥ በአገልግሎት የማይመሳሰሉት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ግመልና ፈረስ　　ሐ. ፈረስና በቅሎ

ለ. አህያና ፍየል　　መ. ሁሉም

# ትምህርት ሶስት፡- መናገር

**ተግባራት** ፡- ሀ.ተማሪዎች ከጓደኞቻችሁ ጋር ተጫውታችሁ ታውቃላችሁ?

ለ.ጭውውት በስንት ሰዎች መካከል የሚካሄድ ይመስላችኋል፡፡ ተናገሩ?

**መልመጃ አንድ፡-**

ተማሪዎች፣ ኡፋይሴና- ዶግሶ ያደረጉትን ጭውውት መሰረት በማድረግ እናንተም በተለያየ ርዕስ ጥንድ ጥንድ በመሆን ጭውውት አድርጉ፡፡

**ማስታወሻ**

- ጭውውት በጓደኛሞች ወይም በሚግባቡ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ የሀሳብ ልውውጥ ነው፡፡
- ጭውውት ሲደረግ አንዱ የሌላውን ሀሳብ በጥሞና ማዳመጥ አለበት፡፡

**ኡፋይሴ-** ዶግሶ፣ የቤት ሥራህን ሰርተሃል?

**ዶግሶ -** የቤት ሥራ ተሰጥቷል እንዴ?

**ኡፋይሴ -** አዎን የአማርኛ መምህርት ነገ አርምላችኋለሁ ብላለች፡፡

**ዶግሶ -** ወይኔ! እስቲ ደብተሬን ልፈትሽ

**ኡፋይሴ** - አንተ የቤት ሥራ የምትሰራበት ፕሮግራም የለህም እንዴ?

**ዶግሶ** - እኔ በፕሮግራም አላጠናም ደስ ባለኝ ሰዓት ነው የማጠናው፡፡

**ኡፋይሴ** - ይህማ ለአንተ ጥሩ አይደልም፡፡ በፕሮግራም ብታጠና ለአንተ ለዘለቄታው ጥሩ ነው ፡፡

**ዶግሶ** - አንቺ በፕሮግራም ነው የምታጠኚው?

**ኡፋይሴ -** አዎን ዶግሶ፤ አንተም በዚሁ መንገድ ብታጠና ውጤታማ እንደምትሆን እርግጠኛ ነኝ፡፡

**ዶግሶ** - በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ እኔም በፕሮግራም አጠናለሁ፡፡

**መልመጃ ሁለት**

**ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

________ 1 ጭውውት በአንድ ሰው ብቻ ሊደረግ ይችላል፡፡

________ 2. በጭውውት ወቅት አንድ ሰው ሃሳቡን ተናግሮ እንስኪጨርስ ማዳመጥ ተገቢ ነው፡፡

________ 3. ጭውውት ሲደረግ መጯጯህ ቢኖርም ችግር የለም፡፡

________ 4. ጭውውት ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥ ነው፡፡

________ 5. በጭውውት ላይ ያልገባን ነገር ካለ መጠየቅ አስፈላጊ አይደለም፡፡

________ 6. ጭውውት በጓደኛሞች ብቻ የሚደረግ ንግግር ነው፡፡

________ 7. ጭውውት የምናደርግበት ጉዳይ የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡

## ትምህርት አራት፡- ማንበብ

**ተግባራት ፡-** ሀ. ቤተሰቦቻችሁ የሚጠቀሙት መጓጓዣ ባህላዊ ነው ወይስ ዘመናዊ ነው? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. ከባህላዊውና ከዘመናዊው የመጓጓዣ አገልግሎት የቱ ይሻላል ትላላችሁ? ለምን?

**ማስታወሻ**

ባህላዊው የመጓጓዣ አገልግሎት ከዘመናዊ ጋር ሲወዳደር ዘገምተኛና አድካሚ ከመሆኑም በላይ ለማድረስ የተፈለገውን ነገር በተፈለገው ጊዜና ሰዓት እንደልብ ለማድረስ ያዳግታል፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ መልዕክት ከዲላ ወደ ጂንካ በፈረስ ወይም በመኪና አሊያም በአውሮፕላን ለማድረስ ብንፈልግ በፈረስ የተላከው አስራ አምስት ቀን ወይም ከዚያም በላይ ሊፈጅ ይችላል፡፡ በመኪና የተላከው ደግሞ ሁለት ቀን ወይም አንድ ቀን ሙሉ ሊወስድበት ይችላል፡፡ በአውሮፕላን የተላከው መልዕክት ግን በአንድና በሁለት ሰዓት ውስጥ ሊደርስ ይችላል፡፡ አውሮፕላን ጉዞው ፈጣን ብቻ ሳይሆን ምቹ እና መልዕክቱንም አስተማማኝ በሆነ መልኩ ሊያደርስ ይችላል፡፡ በፈረስ የተላከው ምን ያህል አሰልቺና አድካሚ ጉዞ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡

# ትምህርት አምስት፡- መፃፍ

ተግባር፡- ተማሪዎች በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ባህላዊ የመጓጓዣ እንስሳት መካከል በጣም ፈጣኑ ማነው ? ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## መልመጃ አንድ

መምህራችሁ የትራፊክ አደጋ ህግን የተመለከተ ጽሁፍ ያነቡላችኂል፡፡ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ካዳመጣችሁ በኂላ ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ደግሞ ሀሰት እያላችሁ በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ከትራፊክ መመሪያ አንዱ የቀይ መብራት አገልግሎት ነው፡፡
2. ግራ ይዞ መሄድ የትራፊክ ህግን ማክበር ነው፡፡
3. ከትራፊክ ህግ አንዱ ዜብራ መንገድ ለእግረኞች የተሠራ ነው፡፡
4. የመኪና መንገድ ስናቋርጥ የቆመ መኪናን ተከትለን ማቋረጥ የለብንም፡፡
5. ዜብራ መንገድ ስናቋርጥ በፍጥነት መሆን አለበት፡፡

## መልመጃ ሁለት

**የሚከተሉትን ቃላት ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ሥሩባቸው፡፡**

**ምሳሌ፡-** ፈረስ፡- ፈረስ የባህል መጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጥ ነው ፡፡

ባጅጅ፡- ባጃጅ ባለ ሶስት ጎማ ዘመናዊ መጓጓዣ ነው፡፡

ሀ. አህያ፡-

ለ. አውሮፕላን፡-

ሐ. በቅሎ፡-

መ. ግመል፡-

ሠ. ባቡር፡-

ረ. መኪና፡-

## ማስታወሻ
### የውሃ ላይ መጓጓዣዎች

የውሃ ላይ መጓጓዣዎች ከየብስ መጓጓዣዎች የሚለዩት፡- አገልግሎታቸው በውሃ ላይ ብቻ የተገደበ በመሆኑ ሲሆን የየብሱ ደግሞ በመሬት ላይ ብቻ የተገደበ ነው፡፡ የየብስ መጓጓዣ የሚባለው ደግሞ ከከተማ ወደ ከተማ፣ ከክልል ወደ ክልል እና ከዞን ወደ ዞን ሊያጓጉዝን የሚችል ነው፡፡ ስለሆነም የውሃ ላይ መጓጓዣዎችን ሁሉም ሰው እንደልብ መጠቀም አይችልም፡፡ ምክንያቱም በሃይቆች፣ በውቅያኖሶች... ወዘተ ላይ ብቻ አገልግሎት ስለሚሰጥ ነው፡፡

## መልመጃ ሶስት

የሚከተሉትን ምስሎች ከስያሜዎቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | " ለ" |
|---|---|
| 1. መርከብ |  |
| 2. አህያ |  |
| 3. ታንኳ |  |
| 4. ግመል |  |
| 5. የጭነት መኪና |  |
| 6. ጀልባ |  |

## ትምህርት ስድስት፡- ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎችን ለይቶ መጻፍ

**ተግባራት፡-** ሀ. በሀገራችን ዘመናዊ መጓጓዣ የምንላቸው ምን ምን ናቸው፡፡ ዘርዝራችሁ ጻፉ፡፡

ለ. ባህላዊ የመጓጓዣ አገልግሎት የሚሰጡትን ዘርዝራችሁ ጻፉ፡፡

### መልመጃ አንድ

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ባህላዊና ዘመናዊ መጓጓዣዎች ስያሜ በመጠቀም በየምድባቸው ለይታችሁ ጻፉ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፈረስ | አውሮፕላን | አውቶብስ | ብስክሌት |
| አህያ | ሂልኮፍተር | መርከብ | ታንኳ (የባህላዊው) |
| በቅሎ | ሞተር ሳይክል | ባቡር | ግመል |
| የጭነት መኪና | ባጃጅ | ፈረስ ጋሪ | የቤት መኪና |

| ባህላዊ መጓጓዣ | ዘመናዊ መጓጓዣ |
|---|---|
| ለምሳሌ፡- በቅሎ | ባጃጅ |
| 1. ________ | 1. ________ |
| 2. ________ | 2. ________ |
| 3. ________ | 3.________ |
| 4. ________ | 4.________ |
| 5. ________ | 5.________ |

## ትምህርት ሰባት፡- ሰዋስው

**ተግባራት ፡- ሀ.** በምዕራፍ ሁለት ላይ የተማራችሁትን በማስታወስ ተውላጠ ስሞች የሚባሉትን ቃላት ዘርዝሩ፡፡

ለ. የስሞችና የተውላጠ ስሞች ልዩነት ምንድን ነው?

### መልመጃ አንድ

**ነጥላና ብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስሞችን ለዩ፡፡**

ምሳሌ፡- ነጠላ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም፡- እኔ

ብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም፡- እኛ

እኔ እኛ

አንተ ፣ አንቺ ፣ እናንተ

እሱ ፣ እሷ ፣ እነርሱ

**መልመጃ ሁለት፡-**

**ቀጥሎ በቀረቡት ተውላጠ ስሞች አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

**ምሳሌ፡- እሱ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡**

ሀ/ እኔ

ለ/ እኛ

ሐ/ እሱ

መ/ እነሱ ( እነርሱ)

ሠ/ እሷ

# ምዕራፍ ስድስት

# የምግብ አይነትና አዘገጃጀት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

### ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ

- በአካባቢያችሁ ስለሚገኙ የምግብ አይነቶችና አዘገጃጀት ትናገራላችሁ፡፡
- የምግብ ዝግጅት ሂደትን በዝርዝር ታስረዳላችሁ፡፡
- በምግብ ጥቅሞች ዙሪያ የተዘጋጁ ምንባቦችን ታነባላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ የምግብ አይነቶችን በዝርዝር ትጽፋላችሁ፡፡
- የተለያዩ የምግብ አይነቶችን አዘገጃጀት በጽሁፍ ታስረዳላችሁ፡፡
- የጎደሉ አረፍተ ነገሮችን በተገቢ ቃላት አሟልታችሁ ትፅፋላችሁ፡፡

## ትምህርት አንድ፡- አዳምጦ መናገር

### የምግብ አይነቶች

**ተግባራት፡- ሀ. የምታውቋቸውን የምግብ አይነቶች ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡**

**ለ. እናንተ የምትወዱት የምግብ አይነት የቱ ነው? ለምን? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡**

## መልመጃ አንድ

ቀጥሎ የቀረቡትን የምግብ አይነቶች ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ አንብቡ።

| | | |
|---|---|---|
| ሽሮ ወጥ | የአበሻ ጎመን | እንቁላል |
| ጎመን በስጋ | ድንች ወጥ | ኩርኩፋ |
| የበቆሎ ገንፎ | ፓስታ | አይብ በጎመን |
| ዶሮ ወጥ | አምባሻ | እንጀራ |
| ቆሎ | ንፍሮ | ቀይ ወጥ |

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደ ጥያቄዎቹ አካሄድ በቃል መልሱ።

ሀ. ከላይ በዝርዝር ከቀረቡት የምግብ አይነቶች ውጪ በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን የምግብ አይነቶችን ተናገሩ።

ለ. ከላይ በቀረበው የምግብ ዝርዝር ውስጥ የማታውቁት የምግብ አይነት ካለ ተናገሩ።

## ትምህርት ሁለት፡- የምግብ አይነቶችን በምድብ ከፋፍሎ መናገር

**ተግባር፡-** ሀ. ሀይል ሰጪ የሚባሉ የምግብ አይነቶች የትኞቹ ናቸው? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ለ. በሽታ ተከላካይ የሚባሉትስ? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

## ማስታወሻ

የምግብ ዓይነቶች ኃይልና ሙቀት ሰጪ፣ ገንቢና በሽታ ተከላካይ በመባል ይመደባሉ፡፡ ኃይልና ሙቀት ሰጪ ከምንላቸው ውስጥ የሚመደቡት ዳቦ፣ ቆጮ፣ ፓስታ፣ ጤፍ ወዘተ ናቸው፡፡

ገንቢ ምግቦች የሚባሉት እንቁላል፣ ባቄላ፣ አደንጓሬ፣ ወተት ወዘተ ናቸው፡፡

በሽታ ተከላካይ ምግቦች የሚባሉት ደግሞ ቃሪያ፣ ሎሚ፣ ብርቱካን፣ ወዘተ ናቸው፡፡

**መልመጃ አንድ**

ከዚህ በታች መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ የምግብ ዓይነቶችን ያነቡላችኋል፡፡ የምግብ አይነት ስሞችን በማዳመጥ ኃይልና ሙቀት ሰጪ፣ ገንቢ ወይም በሽታ ተከላካይ በማለት በቃል መልሱ፡፡

## ትምህርት ሶስት፡- ስለምግብ አዘገጃጀት መናገር

**ተግባራት፡-** ሀ. ቆጮ በልታችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቁ ከሆነ እንዴት እንደሚዘጋጅ ተናገሩ፡፡

ለ. በየአይነት የሚባል ምግብ በውስጡ ምን ምን ነገሮችን ይይዛል? ዘርዝራችሁ ተናገሩ፡፡

**መልመጃ ሁለት**

መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ስለእርጎ አዘገጃጀት የተጻፈ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ እናንተም ምንባቡን በማዳመጥ የሚከተሉትን በስዕል የቀረቡትን የምግብ ዓይነቶች እንዴት እንደሚዘጋጁ በቃል አስረዱ፡፡

ምሳሌ፡- ተራ ቁጥር 3 ከበቆሎ ዱቄትና ከፍርኖ ዱቄት ይዘጋጃል

1.የክፍትፎ ስዕል



2.. የአይብ ስዕል



3. የአምባሻ ስዕል



4.የገንፎ ስዕል



## ትምህርት አራት፡- ምንባብ

### አንብቦ መረዳት

**ተግባራት፡-** ሀ/ ተጠብሰው የሚበሉ የምግብ አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

ለ/ የእንስሳት ተዋጽኦ የሚባሉትን የምግብ አይነቶችን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

### ማስታወሻ

ምግብ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል በሽታ ተከላካይ የሚባሉ ናቸው፡፡ እነዚህም አትክልትና ፍራፍሬዎች ሲሆኑ በጥሬነታቸው የሚበሉ ወይም ተጠብሰው የሚበሉም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ጎመን፣ ሰላጣ፣ ቃሪያ ይጠቀሳሉ፡፡

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ጉልበትና ሙቀት ሰጪ ምግቦችን ይይዛል፡፡ በዚህ ክፍልም የእህልና ጥራጥሬ ዘሮች ናቸው፡፡ ከነዚህ የምግብ ክፍሎች ውስጥ ዳቦ፣ እንጀራ፣ ቂጣ፣ ገንፎ፣ ስንዴ፣ ባቄላ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ አደንጓሬ፣ ቆሎ፣ አተር፣ ወዘተ… ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ሰውነትን የሚጠግኑ የምግብ ክፍሎች ደግሞ በአብዛኛው የሥጋ ክፍሎች ናቸው፡፡ የበግ ስጋ፣ የፍየል ስጋ፣ የዶሮ ስጋ እንዲሁም የአሳማ ስጋ ናቸው፡፡

ለአካል እድገትና ለአካል ግንባታ እንዲሁም ለአጥንቶቻችንና ለጥርሶች ጥንካሬ ጠቃሚ የሚባሉት የወተት ክፍሎች ናቸው፡፡ እነዚህ የወተት ተዋጽኦ የሆኑት በፕሮቲን የበለጸጉ በመሆናቸው ለአካል እድገትና ግንባታ ጠቃሚ ናቸው፡፡

**መልመጃ አንድ**

ከዚህ በታች ከላይ በቀረበው ማስታወሻ ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱን ጥያቄ በምንባቡ መሰረት መልሱ፡፡

1. ምግብ በስንት ክፍሎች ይመደባል?
2. በጥሬነታቸው የሚበሉ የምግብ ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
3. ጉልበትና ሙቀት ሰጪ ምግቦች የትኞቹ ናቸው?
4. አደንጓሬና አተር በየትኛው የምግብ ክፍል ይመደባሉ?
5. አይብ ከምን ይገኛል?

## ትምህርት አምስት፡- የምግብ ክፍሎችን ማዛመድ

**መልመጃ አንድ**

**በ ”ሀ” ክፍል ለቀረቡ የምግብ ክፍሎች ከ “ለ” ክፍል ጋር አዛምዱ፡፡**

| ”ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. በሽታ ተከላካይ | ሀ. ሙዝ፣ ብርቱካን |
| 2. ጉልበትና ሙቀት ሰጪ | ለ. የበግ ሥጋ፣ የፍየል ሥጋ |
| 3. ሰውነት የሚጠግኑ | ሐ. የወተት ክፍል |
| 4. ለአካል ግንባታ የሚሆኑ | መ. አተር፣ ባቄላ፣ ገብስ |

**መልመጃ ሁለት**

**የሚከተሉትን ሃረጎች አንብባችሁ አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

**ምሳሌ፡-** ሀ. በኘሮቲን የበለጸጉ ምግቦች


በኘሮቲን የበለጸጉ ምግቦች የወተት ክፍሎች ናቸው፡፡

ሀ. በኘሮቲን የበለጸጉ ምግቦች
ለ. ሰውነት የሚጠግኑ ምግቦች
ሐ. የፍየል ሥጋ
መ. የአጥንትና የጥርስ ጥንካሬ

## ትምህርት ስድስት፡- አጫጭር አረፍተ ነገሮችን መጻፍ

**ተግባራት፡- ሀ. ሀይል ሰጪ ምግቦች ምን ምን እንደሆኑ ጻፉ፡፡**

ለ. ወተት ከየትኛው የምግብ ምድብ ውስጥ እንደሚገኝ ጻፉ፡፡




### መልመጃ አንድ

**ሀ. ከላይ የቀረበውን ስዕላዊ መግለጫ በማየት አራት አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡**

**ምሳሌ፡-** ማዕድን ከአትክልትና ከሥጋ ይገኛል፡፡

## ትምህርት ሰባት፡- ዝርዝር አረፍተ ነገሮችን በመጻፍ አንቀጽ መመስረት

### መልመጃ አንድ

ሀ. የሚከተሉት የምግብ አይነቶች እንዴት እንደሚዘጋጁ ሌሎች ሰዎችን ጠይቃችሁ ስለ አዘገጃጀቱ ዝርዝር አረፍተ ነገሮችን በመጻፍ አንቀጽ መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- እንጀራ በምግብነት ከመቅረቡ በፊት ጤፍ ይፈጫል፤ የተፈጨው ዱቄት ይቦካል፤ የተቦካው ይጋገራል፡፡ የተጋገረው እንጀራ በትሪ (በሌሎች ዕቃዎች ) ተደርጎ በምግብነት ይቀርባል፡፡

1.በየአይነት

2.ቆጮ

3.ፓስታ

4.አይብ

5.ቆሎ

ለ. በምሳሌው መሰረት ጥያቄዎችን በጽሁፍ መልሱ፡፡

**ምሳሌ፡-** ድንች ይላጣል፤ ይቀቀላል፤ ይፈጫል፤ ይከተፋል፤ ይበላል፡፡

1.ብርቱካን

2.ወተት

3.ሙዝ

4.ባቄላ

## የአእምሮ ማበልጸጊያ ተግባራት

ሀ. በየቀኑ ምን ምን ዓይነት ምግብ ትመገባላችሁ?

ለ. በየቀኑ የምተምገቡት ምግብ ከየት ከየት ይገኛል?

ሐ. በስዕሉ ላይ የተመለከቱት የምግብ አይነቶች ምንጫቸው ከእንስሳት ወይም ከእፅዋት መሆኑን ጻፉ።






ካሮት

አሳ እንቁላል የተቆረጠ ብርቱካን






ቃሪያ ቲማቲም ገብስ ጥቅል ጎመን




ወተት ስጋ

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ፡- | ከዕጽዋት | ከእንስሳት |
| | ገብስ | ወተት |

# ምዕራፍ ሰባት

# የሙዚቃ መሳሪያዎች

**የሚጠበቁ ውጤቶች፦**

- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በስዕል ተመልክታችሁ ስማቸውን ትናገራላችሁ፡፡
- ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በስዕል ተመልክታችሁ ስማቸውን ትናገራላችሁ፡፡
- የቀረበውን ግጥም በሚና ጨዋታ መልክ ትተገብራላችሁ፡፡
- ጽሁፉን አንብባችሁ ሀሳቡን ትገልጻላችሁ፡፡
- የሙዚቃ መሳሪያዎችን አይነትና አዘገጃጀት ዘርዝራችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- የሙዚቃ መሳሪያዎችን ከተግባራቸው ጋር ታዛምዳላችሁ፡፡
- አረፍተ ነገሮችን ትጽፋላችሁ፡፡

## አዳምጦ መናገር

**ትምህርት አንድ፦ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ስያሜዎችን አዳምጦ መናገር**

**ተግባራት፦**

ሀ.ተማሪዎች ስለ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ሲነገር ሰምታችሁ ታውቃላችሁ የሰማችሁትን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡


ለ. በአካባቢያችሁ ስላሉ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ሐ. ከታች የቀረቡትን የሙዚቃ መሣሪያዎችን ስም ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡


ምሳሌ፡ ሥዕል 4 አርሞኒካ ነው



ስዕል(1)



ስዕል2




ስዕል 3



ስዕል 4



ስዕል (5)



ስዕል (6)



ስዕል (7)



ስዕል (8)

## መልመጃ አንድ

ከላይ የቀረበውን ምስል በማየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡
ምሳሌ፡- በተራ ቁጥር (4) ላይ የቀረበው የሙዚቃ መሣሪያ አርሞኒካ ይባላል፡፡

ሀ. በተራ ቁጥር 4 ላይ የቀረበው ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያ ምን ተብሎ ይጠራል?

ለ. ከቀረቡት ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ውስጥ የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያ የሆነው የቱ ነው?

ሐ. ከቀረቡት የሙዚቃ መሣሪያዎች ውስጥ ባለ አንድ ትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ የሆነው የቱ ነው?

መ. ተራ ቁጥር 7 ላይ የቀረበው የሙዚቃ መሣሪያ ምንድን ነው?

ሠ. ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ የሆነና መሣሪያው በጣት ቅኝት የምንቀኘው የቱ ነው?

ረ. ከቀረቡት የሙዚቃ መሣሪያዎች ውስጥ በጭራ የምንቀኘው የቱ ነው?

## ትምህርት ሁለት፡- ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያ ስያሜዎችን አዳምጦ መናገር

ተግባራት፡- ሀ. ተማሪዎች ስለ ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ሲነገር ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? የሰማችሁትን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. እናንተ የምታውቋቸው ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ካሉ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ሐ.ቀጥሎ የቀረቡትን ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ስማቸውን ተናገሩ፡፡

ምሳሌ ስዕል (2) ፒያኖ ይባላል



ስዕል 1



ስዕል 2



ስዕል 3



ስዕል 4



ስዕል 5

**መልመጃ አንድ**

ከላይ የቀረቡትን ምስሎች በማየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ስዕል 2 ላይ የቀረበው ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያ ምን ይባላል?
2. ከቀረቡት ስዕሎች ውስጥ ዘመናዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያ የሆነው የቱ ነው?
3. ከቀረቡት ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ስዕሎች ውስጥ በብዛት በተለያዩ ሙዚቃዎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለው የቱ ነው?
4. በስዕሉ ከቀረቡት ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ውስጥ ሌላ የምታውቋቸውን ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያ ስሞችን በመዘርዘር ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
5. በስዕሉ ላይ የቀረቡት የሳክስፎን እና ቫይሊን ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በምን በምን እንደሚለያዩ ተናገሩ፡፡

## ትምህርት ሦስት፡- መናገር

### የእንኳን ደስ ያለህ የመልካም ምኞት መግለጫ

ተግባራት፡- ሀ/ በአካባቢያችሁ የመልካም ምኞት መግለጫን የምታቀርቡት ምን ሲሆን ነው? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ/ እንኳን ደስ ያለህ (ሽ) ቢሏችሁ ምላሻችሁ ምንድን ነው? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ሐ. ከዚህ ቀጥሎ ጫክሶ ከሙዚቃ መሳሪያዎች አንዱ የሆነውን ዋሽንት የተሸለመበትን ምክንያት መነሻ አድርጋ ታጸኔ እንኳን ደስ ያለህ የሚልና የወደ ፊት መልካም ምኞት መግለጫ ታቀርባለች፡፡

እናንተም የመልካም ምኞት መግለጫውን ጭውውት ተከታትላችሁ ከዚህ በታች ለቀረቡት መልመጃዎች መልስ ስጡ፡፡



ጫክሶ ታጸኔ

ታጸኔ፡- ጫክሶ ይህን ዋሽንት የገዛልህ ማን ነው?

ጫክሶ፡ - ወንድሜ ነው፡፡

ታጸኔ፡- ዋሽንቱ ዋጋው ስንት ነው?

ጫክሶ፡- ውድ ነው፡፡

ታጸኔ፡- ምን ስለሰራህ ነው ዋሽንቱ የተገዛልህ?

ጫክሶ፡- 4ኛ ክፍል 1ኛ ስለወጣሁ ነው፡፡

ታጸኔ፡- 1ኛ ወጣህ?

ጫክሶ፡- አዎን፡፡

ታጸኔ፡- እንኳን ደስ ያለህ፡፡ 5ኛ ክፍልም 1ኛ እንድትወጣ በርትተህ አጥና
ጫክሶ፡- አመሰግናለው ታጸኔ፡፡
ታጸኔ፡- ምንም አይደለም፡፡

### መልመጃ አንድ

ከላይ የቀረበውን የመልካም ምኞት የሀሳብ ልውውጥን መሰረት አድርጋችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. ዋሽንቱ የተገዛው ለማን ነው?
2. ዋሽንት የተገዛለት ለምንድን ነው?
3. ዋሽንቱን በሽልማት መልክ ያበረከተው ማን ነው?
4. በትምህርቱ አንደኛ የወጣው ማን ነው?
5. በሃሳብ ልውውጡ ውስጥ የመልካም ምኞት መግለጫ ንግግር የሆነው የቱ ነው?

### መልመጃ ሁለት

እናንተም የአንድን ጎበዝ ተማሪ ሞዴል ሆናችሁ ክፍል ውስጥ ጭውውት አድርጉ፡፡

## ትምህርት አራት፡- አዳምጦ መናገር

### የክር እና የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያዎችን አዳምጦ መናገር

**ተግባራት፡-** ሀ. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የክር ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ካሉ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ዘርዝሩ፡፡

## መልመጃ አንድ

**መምህሩ ከመምህር መምሪያ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. በገና መንፈሳዊ ዜማዎችን ለማዜም የሚያገለግል የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡
2. ዱል በጋምቤላ የሚገኝ የጅማት መሣሪያ ነው፡፡
3. ዋሽንት በመድረክ ላይ ለክራርና ለመሰንቆ ቅኝት በመስጠትና ዜማን በማጀብ ያገለግላል፡፡
4. መለከት የክር ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ነው፡፡
5. ጨቻ ዘዬ በደቡብ ኢትዮጲያ ውዝዋዜ ለማድመቅ የሚያገለግል የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

## መልመጃ ሁለት

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በቃል ተናገሩ፡፡**

1. ከበሮ ከየትኛው ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ውስጥ እንደሚመደብ አስረዱ፡፡
2. ነጋሪት የሚባለው የሙዚቃ መሳሪያ አብዛኛውን ጥቅም ላይ የሚውለው በምን ጊዜ ነው?
3. ሦስቱን የእንቢልታ አይነቶችን ግለጹ፡፡

## ትምህርት አምስት፡- የሚና ጨዋታ

### ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ተጠቅሞ ተግባራትን መከወን

**ተግባራት፡-** ሀ. በአካባቢያችሁ የተለመዱ ዜማዎች የሚዜሙት በምን አይነት የሙዚቃ መሳሪያ ነው?

**መልመጃ አንድ**

ቀጥሎ በ"ሀ" ምድብ ውስጥ የቀረበውን ግጥም ክራርና ከበሮ በመጠቀም በሚና ጨዋታ መልክ ተራ በተራ ከውኑ።



እቴ ሜቴ የሎሚ ሽታ
ያ ሰውዬ ምናለሽ ማታ
ምንም፣ ምንም፣ ምንም አላለኝ
ትዳሩን ፈቶ ልውሰድሽ አለኝ
አይወስድሽም ትዳሩን ፈቶ
ምሎልሻል ጋሻ ጦር ደፍቶ
ማላ ማላ የጎበዝ ማላ
ፋት ይላታል እንደጉሽ ጠላ
ከቤቴ በላይ ቁራ ሰፍሮ
ቁራ ሰፍሮ
የለሽም ብሎ ሄዶ በሮ
ሄዶ በሮ
እኔን ያብረኝ ያብረኝ
ያብረኝ
የዝሆን ህሞት ያጠጣኝ
ያጠጣኝ



የዝሆን ሀሞት መራራ ነው

መራራ ነው

የጎበዝ ልቡ ተራራ ነው

ተራራ ነው

ተራራ ሄጄ ስመለስ

ስመለስ

አሕያ ሞቶ ጅብ ሲያለቅስ

ጅብ ሲያለቅስ

ቁንጫ ቆማ ስትቀድስ

ስትቀድስ

እባብ አንገቱን ሲነቅስ

ሲነቅስ

የታረደው ሀምሳ ዶሮ

እሷን ይዤ ጓሮ ለጓሮ

## ትምህርት ስድስት፡- አንብቦ መረዳት

**ተግባር፡-** በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ስሞች በመጥራት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

አቅርቦት፡-ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ስሞችን ማንበብ

| | | |
|---|---|---|
| በገና | መሰንቆ | እምቢልታ |
| ክራር | ዋሽንት | መለከት |
| ከበሮ | አታሞ | ነጋሪት |
| ፅናፅል | ቫየሊን | ቃጭል |
| አርሞኒካ | ጥሩምባ | ፊሽካ |
| ኪይቦርድ | ፒያኖ | ክላርኔት |

## ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች

በኢትዮጵያ ሀገራችን ውስጥ የተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች በመኖራቸው መክንያት የተነሣ በአይነት ተከፍለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች በሦስት አይነት ምድብ ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ እነዚህም የክር፣ የትንፋሽና የምት ተብለው ይከፈላሉ፡፡ **የክር** የምንላቸው ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች በገና፣ ማሲንቆ፣ ክራርና የመሳሰሉት

ናቸው፡፡ **የትንፋሽ** ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች የምንላቸው ደግሞ ዋሽንት፣ ጡሩምባ፣ እምቢልታና የመሳሰሉት መሳሪያዎች ሲሆኑ **የምት** ባህላዊ የሙዚቃ

መሣሪያዎች የምንላቸው ደግሞ ከበሮ፣ ነጋሪት፣ ደውል፣ ፅናፅል፣ ቃጭልና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

እስከ አሁን ካነበባችሁት አንቀጽ ምን ተረዳችሁ?

እነዚህ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች በመሆናቸው በአካባቢው ላይ ከሚገኙ ግብአቶች የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ **የክር** የሚባሉት ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች አብዛኛው የድምፅ ቅኝት የሚሠራው ከጅማት ሲሆን የተቀረው የመሣሪያው ክፍል ከእንጨት ውጤቶች እንዲሁም ከቅል ሊዘጋጁ ይችላል፡፡

ሁለተኛው ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ **የትንፋሽ** ሲሆን ይህ መሣሪያ በአብዛኛው ከቀርከሀ ወይም ከሸምበቆ ሊዘጋጀ ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቅልና ሹል ብረት ለሥራው በግብአትነት ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

ሶስተኛው ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ **በምት** የሙዚቃ መሳሪያ ውስጥ የሚመደብ ሲሆን ይህም ከተለያዩ ቁሳቁሶች ይዘጋጃል፡፡ እነሱም ከከብት ቆዳ፣ ጠፈር፣ ብረት መዳብ፣ እንጨት፣ ነሀስ ከመሳሰሉት ቁሳቁሶች ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በአይነታቸው በሦስት ምድብ ይከፈላሉ፡፡ እነሱም የክር፣ የትንፋሽና የምት ናቸው፡፡ ሦስቱም እንደ አይነታቸው መሣሪያው የሚሰራበት ግብዓትና አገልግሎታቸውም የሚለያዩ ናቸው፡፡

## መልመጃ አንድ

**ከላይ የቀረበውን ምንባብ ካነበባችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ሆሄ ምረጡ፡፡**

1. ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች በስንት ይከፈላሉ?

| | |
|---|---|
| ሀ. በሁለት | ሐ. በአራት |
| ለ. በሦስት | መ. በአምስት |

2. ከሚከተሉት ውስጥ የክር ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ክራር ሐ. ነጋሪት

ለ. ፅናፅል መ. አርሞኒካ

3. የክር የሚባሉት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች በአብዛኛው የድምፅ ቅኝታቸው የሚሠራው ከ ----------------- ነው፡፡

ሀ. ከሲባጎ ሐ. ከጅማት

ለ. ከፈረስ ጭራ ፀጉር መ. ከልብስ ክር

4. ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሣሪያ አብዛኛው የሚሠራው ከምንድን ነው?

ሀ. ከእንጨት ሐ. ከኘላስቲክ

ለ. ከቀርክሀ መ. ከላሜራ

5. ከምት ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ውስጥ የሚመደበው የቱ ነው?

ሀ. ማሲንቆ ሐ. በገና

ለ. ከበሮ መ. ክራር

6. የምት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ከምን ይሠራል?

ሀ. ከከብት ቆዳ ሐ. የፍየል ቆዳ

ለ. ከሸንበቆ መ. ከበግ ቆዳ

7. ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ድምፅ ያለው መሣሪያ ከየትኛው ምድብ ውስጥ ነው?

ሀ. ከክር ለ. ከምት ሐ. ከትንፋሽ

## ትምህርት ሰባት፡- መጻፍ

### ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን አይነትና አዘገጃጀት መጻፍ

**ተግባራት፡- ሀ. ተማሪዎች፣ የአካባቢያችሁን ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ አዘገጃጀት ለመምህራችሁ በጽሁፍ አሳዩ፡፡**

**ማስታወሻ፡-**

## የመሰንቆ አዘገጃጀት

መሰንቆ ከክር የሙዚቃ መሳሪያ ምድብ ከሚመደቡ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ መሰንቆ ለማዘጋጀት ብዙ የፈረስ ጭራዎች አንድ ላይ **ይሸረባሉ**፡፡ በመቀጠልም ሳጥን መሰል ነገር ከጣውላ እንጨት ይዘጋጃል፡፡ ድምፅም እንዲያወጣ በፍየል ቆዳ **ይለጎማል**፡፡ በተጨማሪም በሳጥኑ በአንደኛው ማዕዘን ውስጥ ቁልቁል አንድ ቋሚ እንጨት ይገባል፡፡ በቋሚው እንጨት ላይ የፈረስ ጭራው ይወጠራል፡፡ ሌላ ደጋን የመሰለ እንጨት ይዘጋጃል፡፡ በዚህ እንጨት ላይ የፈረስ ጭራ ይወጠራል፡፡ የተወጠረው የፈረስ ጭራ ጥቅሙ ልክ እንደጅማት ድምፅ እንዲወጣ ነው፡፡

**መልመጃ አንድ**

ልጆች ከላይ ስለ መሰንቆ አዘገጃጀት የቀረበውን ማስታወሻ ተመልክታችሁ ቀጥሎ የቀረቡት ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች እንዴት እንደሚዘጋጁ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ከበሮ | 3. ክራር |
| 2. ፅናፅል | 4. ዋሽንት |

**መልመጃ ሁለት**

ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገሩን አሟሉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዋሽንት | መሰንቆ | ከበሮ | ክራር |

1. --------------------- የክር ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ በመባል ይታወቃል፡፡
2. ---------------------- የበሬ ቆዳ በመወጠር የሚዘጋጅ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያ ነው፡፡
3. ---------------------- የድምፅ ቅኝቱ የሚሠራው በፈረስ ጭራ ነው፡፡
4. ---------------------- ከምት የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚመደብ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡
5. ---------------------- የሙዚቃ መሣሪያ ከሸንበቆ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

**መልመጃ ሶስት**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምሳሌዎቹን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ጻፉ፡፡

1. ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ስም ጻፉ፡፡
2. ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ስያሜ ተጠቅማችሁ ሐረግ መስርቱ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ፡- | በገና ፤ | ፒያኖ ፤ | ከበሮ ፤ ነጋሪት |

ምሳሌ፡- በገና መደርደር

1. ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ስያሜዎች ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- አበበ በገና ደረደረ፡፡
ዘበርጋ ከበሮ ደለቀ፡፡

# ምዕራፍ 8

# ባህላዊና ዘመናዊ ጨዋታዎች

**የሚጠበቅ ውጤት፡**

- በሥዕላዊ መግለጫዎች ወይም በፎቶ ግራፍ የቀረቡላችሁን የባህላዊና ዘመናዊ ጨዋታ ዓይነቶች ተመልክታችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ባህላዊና ዘመናዊ የጨዋታ ዓይነቶችን በሚገልፁ ቃላት ሀረጎችና አረፍተ ነገሮችን መስርታችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ባህላዊና ዘመናዊ የጨዋታ ዓይነቶችን የያዘ ጽሁፍ አንብባችሁ ሀሳቡን ትገልጻላችሁ፡፡
- የዘመናዊ ጨዋታ ዓይነቶችን ዝርዝር አስተካክላችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ያልተሟሉ አረፍተ ነገሮችን አሟልታችሁ ትፅፋላችሁ፡፡

## አዳምጦ መናገር

## ትምህርት አንድ፡- ባህላዊና ዘመናዊ ጨዋታዎችን አተገባበር አዳማጦ መናገር

**ተግባራት፡-**

ሀ/ በአካባቢያችሁ የምታወቁትን ባህላዊ ጨዋታዎች ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ/ እናንተ የምትወዱትን ባህላዊ ጨዋታ ካለ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

አቅርቦት፡ ባህላዊና ዘመናዊ ጨዋታ



ስዕል 1.



ስዕል 2.



ስዕል 3.



ስዕል 4

## መልመጃ አንድ

ከፍ ሲል የቀረበውን ሥዕል ተመልክታችሁ ለጥያቄው ትክክለኛውን መልስ ተናገሩ፡፡

1. በሥዕል ሶስት ላይ ያያችሁት የባህል ጨዋታ ምን ይባላል?
2. የከረንቡላን ሥዕል የሚያሳየው ስንተኛው ተራ ቁጥር ላይ ያለው ነው?
3. የገበጣ ጨዋታ ጉድጓድ ውስጥ የሚጫወቱት በምንድን ነው?
4. ዘመናዊ ጨዋታዎችን ከከተማ ውጪ ማግኘት ይቻላል?

## ትምህርት ሁለት፡- ባህላዊ ጨዋታ

**ተግባር፡-**

ሀ/ ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የምታውቁትን የባህላዊ ጨዋታ ዓይነት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ/ የገበጣ ጨዋታ ከምን ከምን እንደሚሰራ ተናገሩ፡፡



**ማስታወሻ**

1. **የመጫወቻ ገበጣ፡-**

ገበጣ የውድድር መንፈስ የሚታይበት፤ አሸናፊና ተሸናፊ የሚለይበት ባህላዊ ጨዋታ ነው፡፡ ለመጫወቻ የሚያገለግል ገበጣን እንደየ አካባቢው ሁኔታ በተለያዩ ቁሳቁሶች ማዘጋጀት ይቻላል፡፡

**ለምሳሌ፡-**

--- በመሬት ላይ ጉድጓድ በመቆፈር፣

---- ወፍራም ጣውላ በመቦርቦር፣

---- አሸዋና ሲሚንቶ በማቡካት በማዘጋጀት፣

---- ጭቃ አቡክቶ በመጠፍጠፍና በመቦርቦር፣

**2. የመጫወቻ ጠጠሮች ፡-**

የመጫወቻ ጠጠሮችን በአካባቢው ከሚገኙና ከተለያዩ ነገሮች በክብ/በድቡልቡል ቅርጽ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡

**ለምሳሌ፡-** --- ከወንዝ ከሚገኙ ጠጠሮች

--- ከተለያዩ የዛፍ ፍሬዎች፣

---- ከብረት ከሚዘጋጁ ድቡልቡሎች፣

- **የገበጣ መጫወቻ የሚይዘው ጉድጓድ መጠን አስራ ስምንት ነው፡፡**

## መልመጃ አንድ

**ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. የገበጣ መጫወቻ ጉድጓዶቹ አራት ናቸው፡፡
2. በገበጣ ጨዋታ ማሸነፍና መሸነፍ አለ፡፡
3. በገበጣ ጨዋታ ወቅት ተሸናፊው ተሸንፏል የምንለው ጠጠሮቹን ጠቅላላ ሲበላ ነው፡፡
4. ሰዎች ገበጣን ሲጫወቱ ህብረትን ለመፍጠር እንጂ ለጥላቻ አይደለም፡፡

## መልመጃ ሁለት

ከታች የተዘረዘሩትን የጫዎታ አይነቶች አንብባችሁ በምሳሌው መሠረት በየምድባቸው አስቀምጡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ከረንቡላ | ፑል | ሆያ ሆዬ |
| ቼዝ | ፈረስ ጉግስ | እቴ እሜቴ |
| መሀረቤን ያያችሁ | ዱላ ቅብብል | ሰኞ ማክሰኞ |
| ድንቡሼ ገላ | ትግል | ድብብቆሽ |

ሀ/ ዘመናዊ

ለምሳሌ፡ 1.ከረንቡላ

2.________

3._________

4._________

ለ/ ባህላዊ

1.መሀረቤን ያያችሁ

2.___________

3.___________

4.___________

## መልመጃ ሦስት

በአካባቢያችሁ ከላይ ከተጠቀሱት ባህላዊና ዘመናዊ ጨዋታዎች ውጪ የምታውቋቸውን ፅፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ትምህርት ሦስት፡- የዘመናዊ ጨዋታ ስሞችን መናገር

## ተግባር፡-

ሀ/ ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ዘመናዊ የጨዋታ ስሞችን ተናገሩ፡፡

ለ/ ከዘመናዊ ጨዋታ ውስጥ እናንተ መጫወት የምትችሉትን የጨዋታ አይነት ተናገሩ፡፡

## አቅርቦት፡ - ዘመናዊ ጨዋታ



ስዕል 1.



ስዕል 2.



ዐ

ስዕል 3.




ስዕል 4.

**መልመጃ አንድ**

**ከላይ ያለውን ሥዕል ተመልክታችሁ ለጥያቄው ትክክለኛውን መልስ በቃል መልሱ፡፡**

1. ቼዝን የሚጫወቱ ሰዎች ስንት ሆነው ነው?
2. የፑል ጨዋታ ከከረንቡላ በምን ይለያል?
3. ከላይ ከቀረቡት ሥዕሎች ውስጥ በጣም ጉልበት የሚፈልገው የቱ ነው?
4. ከላይ ከሚታዩት ሥዕሎች ውስጥ ቁጭ ብሎ ለመጫወት የሚያስችለው የቱ ነው?
5. ከላይ ከቀረቡት ሥዕሎች ውስጥ የትኛውን መጫወት ትወዳላችሁ? ለምን?

## ትምህርት አራት፡- መፃፍ

**የባህላዊ መጫወቻ መሳሪያዎችን መጻፍ**

**ተግባራት፡ -**

ሀ/ በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን መጫወቻ መሳሪያዎች በዝርዝር ፃፉ፡፡

ለ/ አካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ባህላዊ ጨዋታዎችና የጨዋታ ህግጋት ጻፉ፡፡

## ማስታወሻ

### የገና ባህላዊ ጨዋታ

የገና ጨዋታ በገና ወቅት የሚከወን የጨዋታ ዓይነት ነው፡፡ ይህንን ጨዋታ ለመጫወት የሚያስፈልጉ ነገሮች፡-

ሀ. የገና ጨዋታ መጫወቻ ዱላ፤ ክብደቱ ከ500-550 ግራም ርዝመቱ ደግሞ ከ100ሴ.ሜ ያልበለጠ ነው፡፡

ለ. የጨዋታው ሩር (ጥንግ)፤ዙሪያው ከ25-30 ሳ.ሜ ክብደቱ ደግሞ 100 ግራም ነው፡፡

ሐ. የጨዋታው ጎል፤3ሜ. ርዝመት፤1ሜ.ቁመት ነው፡፡

መ. የጎል መረብ ናቸው፡፡

## መልመጃ አንድ

**በማስታወሻው መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1.የገና ጨዋታ ዱላ ክብደት ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?

ሀ. ከ600-650 ገራም ሐ.ከ60-65 ግራም

ለ.ከ500-550 ግራም መ. 50-55 ግራም

2.የጨዋታው ሩር (ጥንግ) ዙሪያው ስንት ነው?

ሀ. 25-30 ሴ.ሜ ለ. ከ30-35 ሴ.ሜ

ሐ. ከ40-45 ሳ.ሜ መ. ከ10-15 ሳ.ሜ

3.የጨዋታው ጎል ርዝመት________________ነው፡፡

ሀ. 2ሜ. ቁመት ለ. 1ሜ. ቁመት

ሐ. 4ሜ. ቁመት መ. 3ሜ. ቁመት

4.የገና መጫወቻ ሩር (ጥንግ) ክብደቱ ________________ **ነው፡፡**

**ሀ.**100 ግራም ሐ.200 ግራም

**ለ.**150 ግራም መ. መልስ የለም

5. የገና ጨዋታ የሚካሄደው መቼ ነው?

ሀ. በፋሲካ ወቅት ሐ. በገና ወቅት

ለ. ለእንቁጣጣሽ መ. ዓመቱን ሙሉ

## መልመጃ ሁለት

የ "ሀ"ን ክፍል ከ "ለ" ክፍል ጋር አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | "ለ" |
| --- | --- |
| 2. የገና ጨዋታ ጎል ርዝመት | ሀ. ከ500-550 ግራም |
| 3. የገና ጨዋታ ዱላ ርዝመት | ለ. ከ100 ሴ.ሜ ያልበለጠ |
| 4. የገና ጨዋታ ሩር(ጥንግ) | ሐ. 600-650 |
| 5. የገና ጨዋታ ዱላ ክብደት | መ. 4ሜ. |
| | ሠ. 3ሜ |
| | ረ. 100 ግራም |

## ትምህርት አምስት፡- ቃላት

**ተግባር፡- ሀ. ሲጠብቁና ሲላሉ የተለያየ ፍች የሚሰጡ ቃላትን ጻፉ፡፡**

### ማስታወሻ

ቃላት በማጥበቅና በማላላት እንዲሁም በተመሳሳይና ተቃራኒ የተለያየ ትርጉም ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

ቃላት በማጥበቅና በማላላት ሲተረጎሙ በቃሉ ውስጥ ካሉ ፊደላት አንዱ ጠብቆ ወይም ላልቶ በመነበቡ ምክንያት የተነሳ ሁለት የተለያየ ትርጉም ሊኖረው ይችላል፡፡

ምሳሌ፡- ዋና-- አለቃ፣ የበላይ (ሲጠብቅ)

ዋና - መዋኘት ወይም ውሃ ዋና (ሲላላ)

ሰባ - ጮማ ሆነ (ሲጠብቅ)

ሰባ- 70 ቁጥር (ሲላላ)

ቃላት በተማሳሳይ ሲተረጎሙ ተቀራራቢ ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

ለምሳሌ፡- በላ - ተመገበ

ሄደ - ተጓዘ

እንዲሁም ቃላት በተቃራኒ ሲተረጎሙ የቃሉን ተቃራኒ ሀሳብ ያመለክታሉ፡፡

ለምሳሌ: - በላ - ጠጣ

ሄደ - መጣ

## መልመጃ አንድ

ሀ. የሚከተሉት ቃላት ሲጠብቁ የሚሰጡትን ትርጉም ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡- አዳኝ ፡-ሲጠብቅ---- አሳዶ የሚይዝ

1. ትዳር ________________
2. ፍራሽ ________________
3. በላ ________________
4. ጠላ ________________
5. ገና ________________
6. በሽታ ________________

**ለ. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ሲላሉ የሚሰጡትን ትርጉም ፃፉ፡፡**

**ምሳሌ፡-** ሲላላ ----- የሚፈውስ፣ የሚያድን

1. በላ ------------------------------------------
2. ገና------------------------------------------
3. ትዳር------------------------------------
4. አያት------------------------------------
5. ነጻ---------------------------------------

## ትምህርት ስድስት፡- ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍች መስጠት

### መልመጃ አንድ

**ሀ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ።**

1. ሄደ -------------------------------------
2. በላ -------------------------------------
3. አየ -------------------------------------
4. ተቀመጠ -------------------------------
5. ተመኘ -----------------------------------

**ለ. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒያቸውን ስጡ።**

1. ተኛ ---------------------------------------------
2. ቀዳ ----------------------------------------------
3. ወሰደ --------------------------------------------
4. ሄደ -------------------------------------------------
5. ሞላ -------------------------------------------

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# አካባቢያችን

**የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

**ተማሪዎች፣ ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፤**

- አካባቢያችሁን በሚመለከት ለሚቀርብላችሁ ጥያቄዎች መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- አካባቢን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ሀሳብ ትለዋወጣላችሁ፡፡
- ምንባቡን አንብባችሁ መልመጃዎችን ትሰራላችሁ፡፡
- አካባቢን በሚመለከት የሚነበብላችሁን ጽሁፍ አዳምጣችሁ መልዕክቱን ትጽፋላችሁ፡፡
- ስለአካባቢያችሁ አጠቃላይ ሁኔታ ትጽፋላችሁ፡፡
- የአካባቢ ብክለትን የሚያስከትሉ መንስኤዎችን በንግግርና በጽሁፍ ትገልጻላችሁ፡፡
- የሰውነት ክፍሎችን ስያሜ ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- ስለአካባቢያችሁ የሚገልጽ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡

## ትምህርት አንድ፡- አዳምጦ መናገር

### ስለአካባቢያቸው ገጽታ አዳምጦ መናገር

ተግባራት፡- ሀ) ተማሪዎች ስለአካባቢያችሁ አጠቃላይ ገጽታ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ) የአካባቢ ደህንነት ማለት ምን ማለት ነው? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

### መልመጃ አንድ

መምህራችሁ አካባቢን የተመለከተ ምንባብ ያነቡላችኋል ምንባቡን በጥሞና አዳምጣችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡

1.አካባቢ ማለት ምን ማለት ነው? ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ፡፡

2.አካባቢያችን ያማረ እና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ምን መደረግ አለበት?

3.የአንድ አካባቢ ደህንነት የተጠበቀ ነው የምንለው ምን ሲሆን ነው?

4.መምህራችሁ በንባብ ያስደመጧችሁን ጽሁፍ መልሳችሁ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ትምህርት ሁለት፡- ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ ያለውን ፋይዳ መናገር

ተግባራት፡- ሀ) ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ ጥቅሙ ምንድን ነው? ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ) ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ ገጽታ ምን አይነት ነው?

**መልመጃ አንድ**

ሀ) መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1.የምንኖርበት አካባቢ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ምን ምን ነገሮችን መያዝ አለበት?

2.በቂ የሆነ የውሃ አቅርቦት የሌለው አካባቢ ምን አይነት ችግሮችን ሊያስተናግድ ይችላል?

3.አየሩ በተበከለ አካባቢ መኖር በጤና ላይ ምን አይነት ጉዳት ያደርሳል?

## ትምህርት ሶስት፡- የአካባቢ ብክለት የሚያስከትለውን መንስኤ መናገር

ተግባራት፡- ሀ) የአካባቢ ብክለት ማለት ምን ማለት ነው?

ለ) የአካባቢ ብክለት መከሰቻ መንገዶቹ ምን ምን ናቸው? የምታውቁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ሐ) የአካባቢ ብክለት የሚፈጠረው በምን በምን ምክንያት ነው?

**መልመጃ አንድ**

ከዚህ ቀጥሎ አካባቢን የተመለከቱ የተለያዩ ስዕሎች ቀርበዋል፡፡ ስዕሎቹን በአጽንኦት ተመልክታችሁ የሚያስተላልፏቸውን መልዕክት ተናገሩ፡፡



**(ስዕል አንድ)**



**(ስዕል ሁለት)**



(ስዕል ሶስት )

1.የአካባቢ ብክለት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ስዕሎቹን ምሳሌ በማድረግ አስረዱ፡፡

2.በሶስቱ ስዕሎች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በቡድን ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

## ትምህርት አራት፡- የአካባቢ ብክለት የሚያስከትለው ችግር

**ተግባራት፡-** ሀ) አካባቢያችንን የሚበክሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው፡፡ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ?

**መልመጃ አንድ**

ሀ) መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ ሲያነቡላችሁ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የአካባቢ ብክለት መከሰቱን የምናውቀው በምንድን ነው?

ለ) መምህራችሁ የሚያነቡትን ምንባብ መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1)የአካባቢ ብክለት ሊከሰት የሚችለው በምን ምክንያት ነው?

2)የአካባቢ ብክለት መከሰት የሚያመጣው ችግር ምንድን ነው?

3)የአካባቢ ብክለት የሚያመጣው ችግር በምን በምን ላይ ነው?

4)የአካባቢ ብክለትን መቀነስና ማጥፋት ይቻላል ብላችሁ ታስባላችሁ? እንዴት?

## ትምህርት አምስት፡- የአካባቢ ብክለት መከላከያ ዘዴዎችን መናገር

ተግባራት፡- ሀ) አካባቢ ከብክለት የጸዳ እንዲሆን መፍትሄው ምንድን ነው?

ለ) አካባቢ ቢበከል በምን አይነት መንገድ ሊጸዳ ይችላል?

### ማስታወሻ

የአካባቢ ብክለትን መቀነሻ ዘዴዎች፡-

✔ስለአካባቢ ብክለት ግንዛቤ መፍጠር፤

✔አካባቢን መልካም ገጽታ እንዲኖረው በሚገባ ማጽዳት፤

✔ጽዱና ምቹ አካባቢን ከመፍጠር አንጻር የግንዛቤ ማስጨበጫ የልምድ ልውውጥ ማዘጋጀት፤

✔አረንጓዴ አሻራን ከመፍጠር አንጻር የተለያዩ ችግኞችን መትከልና መንከባከብ፤

✔በተለያየ አካባቢ የሚኖር ማህበረሰብ አካባቢውን እንዲንከባከብና ጽዱ እንዲያደርግ ማበረታታት፤

✔የአካባቢ ብክለት መከሠቻ መንስኤዎችን መለየትና ለችግሩ አፋጣኝ መፍትሄ መውሰድ፤

**መልመጃ አንድ**

ከላይ በዝርዝር የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በቃል መልሱ፡፡

1. አካባቢን ሊጎዱ ከሚችሉ ነገሮች ውስጥ አንዱን ተናገሩ፡፡
2. የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስ መደረግ የሚገባቸውን ጉዳዮች ተናገሩ፡፡
3. የአካባቢ ብክለትን ልንከላከል የምንችልባቸውን ተግባራት ዘርዝሩ፡፡
4. የአካባቢን ችግሮች ለመፍታት ብሎም ማራኪና ምቹ አካባቢን ለመፍጠር ምን መደረግ አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?
5. የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል ቤተሰቦቻችሁ ሊያከናውኑ ስለሚችሉት ተግባራት በቡድን ሆናችሁ ተነጋገሩ፡፡

## ትምህርት ስድስት፡- መናገር

### የተለያየ ገጽታ ያላቸውን አካባቢዎች ልዩነታቸውን በንጽጽር መናገር

**ተግባራት፡-** ሀ) የምትኖሩበትን አካባቢ ከሌሎች አካባቢዎች ጋር በማወዳደር አንድነትና ልዩነቱን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

አቅርቦት፡- የአካባቢዎችን ገጽታ ልዩነት የሚያሳይ ስዕል



ስዕል አንድ



ስዕል ሁለት

## መልመጃ አንድ

**የሚከተሉት ጥያቄዎች ከታች የቀረቡትን ምስሎች መሠረት ያደረጉ ናቸው። ምስሎቹን በአጽንኦት በመመልከት ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ተናገሩ።**

1.አረንጓዴ ገጽታ ያለው ምስል የትኛው እንደሆነ ግለጹ።

2.የበረሃማነት ገጽታ ያለው ምስል ስንተኛው ላይ ያለው ነው? ይህን በምን ልተለዩ ቻላችሁ? ተናገሩ።

3.በረሃማነት እንዴት ሊከሰት ይችላል ብላችሁ ታስባላችሁ? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ።

4.አረንጓዴ ገጽታን የተላበሰና በተራራማ የተከበበው አካባቢ ምድብ ስንት ላይ ያለው ስዕል እንደሆነ ግለጹ።

5.ሜዳማ ገጽታ ያለው አካባቢ በየትኛው ምድብ የቀረበውን ስዕል እንደሚወክል ተናገሩ።

6.ተማሪዎች እናንተ የትኛውን ስዕል ወደዳችሁ? ለምን? ሀሳባችሁን ምክንያታዊ በሆነ መልኩ አስረዱ።



(ስዕል አንድ)



(ስዕል ሁለት)



(ስዕል 3)



(ስዕል 4)

## ትምህርት ስባት፡- ማንበብ

### አካባቢን የሚገልጽ ጽሁፍ ማንበብ

ተግባር፡- ተማሪዎች እናንተ የምትኖሩበት አካባቢ ገጽታው ምን እንደሚመስል ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው፡፡

**አካባቢን ከብክለት መጠበቅ**

አካባቢ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ሊበከል ይችላል፡፡ የአካባቢ መራቆት አንዱና ዋነኛው ጉዳይ ነው፡፡ ሰዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በዙሪያቸው ያሉትን ደኖች በመመንጠር አካባቢያቸውን ያራቁታሉ፡፡ በርካታ ቁጥር ያላቸውን የቤት እንስሳትን ያሠማራሉ፡፡ ይህ ደግሞ የመሬቱን ደህንነት ሊጎዳና አካባቢውን ምድረ በዳ እንዲሆን አሉታዊ ተፅእኖ ይፈጥራል፡፡ ስለዚህም ዛፎችን ባለመቁረጥ፣ የተለያዩ ችግኞችን በመትከል፣ አካባቢያችን አረንጓዴና ለምለም የሆነ ገጽታ እንዲኖረው በማድረግ ከብክለት የጸዳ አካባቢን መፍጠርና መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

ሌላው አካባቢ በተለያዩ ተረፈ ምርት በሆኑ ቆሻሻዎች ምክንያት የተነሳ ይበከላል፡፡ እነዚህን ተረፈ ምርቶች በየቦታው ከመጣል ይልቅ እራሱን የቻለ ቦታ በማዘጋጀት ቆሻሻውን ማስወገድ ተገቢነት አለው፡፡ እንዲሁም በየቦታው ከመጸዳዳት በመቆጠብ አካባቢያችን ውብና ጽዱ ገጽታን በማላበስ አካባቢያችንን ከብክለት መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

**ከላይ የቀረበውን ምንባብ በግል አንብቡና ከአካባቢያችሁ ገጽታ ጋር በማነጻጸር በቡድን ተነጋገሩ፡፡**

**መልመጃ አንድ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ለአካባቢ መበከል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ምክንያቱ እኛው ነን፡፡
2. የተለያዩ ችግኞችን በመትከልና በመንከባከብ አካባቢን ከብክለት መጠበቅ እንችላለን፡፡
3. ደኖችን መጨፍጨፍ የአካባቢ ብክለትን ያስከትላል፡፡
4. የተለያዩ ተረፈ ምርቶችን በየቦታው ማስወገድ የአካባቢ ብክለትን ይቀንሳል፡፡

## ትምህርት ስምንት፡- መጻፍ

### ስለአካባቢ ገጽታ መጻፍ

**ተግባራት፡-** ሀ) ስለምትኖሩበት አካባቢ ገጽታ ለጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው፡፡

ለ) ተማሪዎች ስለ ቤታችሁና መንደራችሁ የሚገልጽ ውይይት አዘጋጁና ተነጋገሩ፡፡

**አቅርቦት ፡- የተጎዳ መሬት**



( ስዕል 1)

**መልመጃ አንድ**

**ከላይ የቀረበውን ስዕል መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡**

1.ከላይ የቀረበውን ስዕል በመመልከት ስለ አካባቢው ሁኔታ ጻፉ፡፡

2.አካባበቢያችንን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል አጭር ጽሁፍ አዘጋጁ፡፡

3.የምትኖሩበትን አካባቢ ገጽታ እንደሚመስል በጽሁፍ አቅርቡ፡፡

4.አካባቢያችን ውብና ማራኪ የሆነ ገጽታ እንዲኖረው ምን መደረግ እንዳለበት በጽሁፍ አዘጋጁ፡፡

5.የአካባቢ ጥበቃ መጓደል የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽዕኖ የሚመለከት ጽሁፍ በማዘጋጀት ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ትምህርት ዘጠኝ፡- ሰዋስው

### የሰውነት ክፍሎችን ስያሜ ተጠቅሞ አረፍተ ነገር መመስረት

**ተግባር፡-** አረፍተ ነገር በመመስረት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**አቅርቦት፡-** የሰውነት ክፍሎችን መሠረት ያደረገ አረፍተ ነገር፡፡

**ምሳሌ፡-** ጆሮ ድምጾችን የምንለይበት ነው፡፡

አዕምሮ ነገሮችን ማገናዘቢያ ክፍል ነው፡፡

**መልመጃ አንድ**

**ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ተጠቅማችሁ አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ጸጉር | ምላስ | አንገት |
| አፍንጫ | እጅ | ኩላሊት |
| አፍ | ሆድ | ልብ |
| ጥርስ | እግር | |

**መልመጃ ሁለት**

**ተማሪዎች አካባቢያችሁን የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

# ምዕራፍ አሥር

# ተረት

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- ካዳመጣችሁት ተረት ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ቃላት ታነባላችሁ፣ ትጽፋላችሁ፡፡
- ተረትን አዳምጣችሁ የተረዳችሁትን መልሳችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ትጽፋላችሁ፣ ታነባላችሁ፡፡
- በተረት ውስጥ ያሉ ገጸባህርያትን ለይታችሁ ትናገራላችሁ፡፡

## ትምህርት አንድ፡- አዳምጦ መናገር

### ተረትን አዳምጦ ጥያቄዎችን መመለስ

ተግባር፡- የምታውቁትን ተረት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**መልመጃ አንድ**

**ሀ. ከዳመጣችሁት ተረት ተነስታችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. በተረቱ ውስጥ ስለችግሮቻቸው የተወያዩት ምኖች ናቸው?
2. የዛፎቹ ትልቁ ችግር ምንድን ነው?
3. ተቃውሞ ያቀረበው ማን ነበር?
4. የተጨበጨበለት ማን ነው?
5. ያጨበጨቡለትስ እነማን ናቸው?

ለ.ካዳመጣችሁት ተረት ተነስታችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በቃል ተናገሩ፡፡

ሀ. የደን መመንጠር በሰው ልጆች ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ምንድን ነው?

ለ. ሁሉም ዛፍ ቀጥ ብሎ ቢያድግ መጥረቢያ ከየት ይገኝ ነበር?

ሐ. ጠላታችን መጥረቢያ ሳይሆን እኛው እራሳችን ነን ያለው ምን ለማለት ፈልጎ ነው፡፡

## ትምህርት ሁለት፡- ከተረት ውስጥ አዳዲስ ቃላትን ለይቶ ማውጣት

ተግባር፡- ተማሪዎች ተረት ስታዳምጡ ምን ምን ነገሮችን ትማራላችሁ?

**መልመጃ አንድ**

**መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ተረት አዳምጣችሁ ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡**

ሀ) ካዳመጣችሁት ተረት ውስጥ የምታስታውሷቸውን አዳዲስ ቃላት ተናገሩ?

ምሳሌ፡- ዘላን፣ በረት፣ መንጋ፣ እንቦሳ

ለ) ያዳመጣችሁትን ተረት በማስታወስ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

ሀ.ጅቡ እምቦሳውን በልቶታል፡፡

ለ. ከብት አርቢ ዘላን ይባላል፡፡

ሐ.ጅቡ እምቦሳዋን ፈርቶ ሲሸሽ ደክሞት ወድቋል፡፡

መ.ከብት አርቢው ጅቡን በጦር ገድሎታል፡፡

## ትምህርት ሶስት፡- ማንበብ

### ከሚነበብ ተረት የአዳዲስ ቃላትን አገባብ መረዳት

**ተግባር፡-** ሀ. ጓደኞቻችንን መርጠን እንያዝ በሚለው ተረት ውስጥ ስለምን ይነሳል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ለ. ጓደኛ መርጦ መያዝ ተገቢ ነው ትላላችሁ? ሀሳባችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አጋሩ፡፡

### ጓደኞቻችንን መርጠን እንያዝ

በአንድ አካባቢ የሚኖር ኀበዝ ገበሬ ነበር፡፡ ይህም ገበሬ እርሻውን በደንብ አርሶና ተንከባክቦ ስለሚይዝ ብዙ ምርት ያመርት ነበር፡፡ ይሁንና አዕዋፍ የተዘራውን እህል እየበሉ ያስቸግሩታል፡፡ ይህንን ችግር ለማስወገድ እንዲቻል በርካታ ወጥመድ አዘጋጀና በየቦታው አስቀመጠ፡፡ በወጥመዱ በርካታ አዕዋፍ ተይዘው አገኘ፡፡ ከአዕዋፋቱም መካከል " **ሺመላ**" የተባለው የወፍ ዝርያ ተይዞ ነበር፡፡

ይህም ወፍ ሰውየው ሊወስደው ሲመጣ " የተከበሩ ገበሬ ሆይ! እኔ እንደ ሌሎቹ ወፎች ጥሬ አልበላም፡፡ እምመገበው ትላትል ነው፡፡ እስከ ተረቱም " ሺመላ ትል እንጂ ጥሬ አይበላ" እየተባለ ይነገራል፡፡ ከዚህም በላይ ከአዕዋፍ ሁሉ ታማኝና ምንም አይነት ጉዳት የማላደርስ ፍጡር ነኝና እባክዎ መልካም ፈቃድዎ ሆኖ ይልቀቁኝ" በማለት ለመነው፡፡ ገበሬው ግን " አያ ሺመላ ትል እንጂ ጥሬ አይበላ፤ ለመሆኑ ጥሬ ካልበላህ እርሻዬ ውስጥ ከሌሎች አዕዋፍ ጋር ምን ልትሰራ ገባህ?" አለው፡፡

ሺመላውም " ይመኑኝ ጌታዬ! ከእነሱም ጋር አልመጣሁም፡፡ እዚህ ቦታም ያረፍኩት እነሱ ምን እንደሚያደርጉ ለማየት ነው፡፡" ሲል መለሰ፡፡ ገበሬው ግን "ነውን? መልካም፣ እኔ ምንም ይሁን ምን የዘራሁትን እህል እየለቀሙ ከሚበሉና በምርቱ ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ አዕዋፍ ጋር አግኝቼሀለሁ፡፡ ስለዚህ

ታማኝና ቅን ብትሆንም ከጥፋተኞቹ ጋር ተሰልፈህ ተገኝተሃልና ለእነሱ የሚገባው ቅጣት ላንተም ይገባሃል" አለው ይባላል።

**መልመጃ አንድ**

**ሀ) ከምንባብ ለወጡ ጥያቄዎች አጫጭር መልሶችን በቃል ተናገሩ።**

1. ሺመላ የምን ዝርያ ነው?
2. ወጥመድ ያጠመደው ማን ነው?
3. በተረቱ ውስጥ ገበሬው ምን አደረገ?
4. ብዙ ምርት ያመረተው ማን ይመስላችኋል?
5. በወጥመዱ የተያዘው ማን ነው?
6. እናንተ ገበሬውን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

**ለ) ከላይ ከቀረበው ተረት የወጡትን ቃላት ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ አንብቡ።**

| | |
|---|---|
| ሺመላ | አዕዋፍ |
| ምርት | ወጥመድ |
| ሺመላ | ታማኝ |

**ሐ) ካነበባችሁት ተረት የወጡትን ሀሳቦች ደጋግማችሁ ጻፉና አንብቡ።**

- በአንድ አካባቢ የሚኖር ጎበዝ ገበሬ ነበር።
- ይሁንና አዕዋፍ የተዘራውን እህል እየበሉ ያስቸግሩታል።
- ሺመላ የተባለ የወፍ ዝርያ ተይዞ ነበር።
- ሺመላ ትል እንጂ ጥሬ አይበላ።

- ለመሆኑ ጥሬ ካልበላህ እርሻዬ ውስጥ ከሌሎች አዕዋፍ ጋር ምን ልትሰራ ገባህ?

## ትምህርት አራት፡- መጻፍ

### ሰነፍ ተማሪ

አንድ ቀላል ሂሳብ እንኳን የማይገባው ሰነፍ ተማሪ ነበር፡፡ አንድ ቀን ታዲያ መምህሩ ስለመቀነስ እያስተማሩ ሳለ ተማሪው ስላልገባው መምህሩ ምሳሌ ይሰጡት ጀመር፤ እንዲህም አሉት፡፡ “ አምስት በጎች በረት ውስጥ ቢኖርህና አንዱ ሾልኮ ቢያመልጥ ስንት ይቀርሃል? ”

ተማሪው “ ጌታው ኧረ ምንም አይቀረኝም ” አላቸው፡፡ መምህሩም በመበሳጨት “ ይህ እንዴት አይገባህም? “ ብለው ጮሁበት፡፡ ተማሪውም እያለቀሰ “ኧረ ጌታው የበጎችን አመል ጠንቅቄ ነው የማውቀው አንዲቷ ካመለጠች ሌሎቹም ተከትለው ነው የሚጠፉት” አላቸው፡፡

በዚህ ጊዜ መምህሩ ሲስቁ በክፍሉ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በሙሉ ሳቁ፡፡

**ምንጭ፡- ኢትዮጲስ ቁጥር 2 /ገጽ2/**

**መልመጃ አንድ**

ከላይ ያነበባችሁትን ተረት መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. ከላይ ከቀረበው ተረት ያገኛችኋቸውን አዲስ ቃላት ጻፉ፡፡
2. አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡

**ምሳሌ፡-** ሀ.ተረት የማዳመጥ ችሎታን ያዳብራል፡፡

ለ.ተማሪው የበጎችን ባህሪ አውቋል፡፡

3.አንድ አጭር ተረት ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

# ዋቢ መጻሕፍት

ሐመልማል አለሙ፡፡(2012ዓ.ም)፡፡ አጠቃላይ የአማርኛ አጋዥ ከ1ኛ
ክፍል፡፡ ሜጋ ማተሚያ ፊንፊኔ፡፡

ሙሉጌታ ይታየው፡፡ (2008ዓ.ም) ፡፡ የአራተኛ ክፍል አማርኛ እንደ
ሁለተኛ ቋንቋ፡፡ የኢፌድሪ ትምህርት ሚኒስቴር፡፡

ሼፍ ካሱ ሰቦቃና ዮናስ ተፈራ፡፡ (1997ዓ.ም)፡፡ ባርኮት የባህልና
መጠጥ አዘገጃጀት፡፡ Fare East Trading PLC.

በደ.ብ.ብ.ሕ መንግስት የብሔረሰቦች ምክር ቤት፣አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ እና
የጋሞ ጎፋ ዞንባህል፣ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን መምሪያ፡፡ 2008፡፡
የጋሞ፣የጎፋ፣የአይዳ፣የዛይሴ እና የጊዲቾ ብሔረሰቦች የግልና የጋራ
እሴቶች፡፡ ሐዋሳ፡፡

ባየልኝ ጣሰው፡፡(1995ዓ.ም)፡፡ የአኙዋክ ተረቶች፣ ሌሮዎች አችለ ተማሪዎቹ
እንዲስማማ ተደርጎ ተሸሻሽሎየቀረበ፡፡ አዲስአበባ፡፡

አባይነሽ ካሳና አበበ እስጢፋኖስ፡፡ (2007ዓ.ም)፡፡ የአምስተኛ ክፍል አማርኛ
እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት፡፡ የኢትዮጵያ ፌድራላዊ
ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስተር፡፡

ኢትዮጲስ ቁጥር 2 /ገጽ2/

WikiPedia Oct 06, 2021 AM 10 :13,

## የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ሀምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

## የፊደል ቅደም ተከተል

ሀ. የመጀመሪያ ፊደል = ግዕዝ

ሁ. ሁለተኛ ፊደል = ካዕብ

ሂ. ሶስተኛ ፊደል = ሳልስ

ሃ. አራተኛ ፊደል = ራብዕ

ሄ. አምስተኛ ፊደል = ሀምስ

ህ. ስድስተኛ ፊደል = ሳድስ

ሆ. ሰባተኛ ፊደል = ሳብዕ

## የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 1 | ፪ 2 | ፫ 3 | ፬ 4 | ፭ 5 | ፮ 6 | ፯ 7 | ፰ 8 | ፱ 9 | ፲ | 10 |
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | 100 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፻ | 100 | ፼ | 10000 |
| ፪፻ | 200 | ፪፼ | 20000 |
| ፫፻ | 300 | ፫፼ | 30000 |
| ፬፻ | 400 | ፬ ፼ | 40000 |
| ፭፻ | 500 | ፭፼ | 50000 |
| ፮፻ | 600 | ፮፼ | 60000 |
| ፯፻ | 700 | ፯፼ | 70000 |
| ፰፻ | 800 | ፰፼ | 80000 |
| ፱፻ | 900 | ፱፼ | 90000 |
| ፲፻ | 1000 | ፲፼ | 100000 |

| የቀናት ስያሜ በአማርኛ | | የቀናት ስያሜ በግዕዝ |
|---|---|---|
| ሰኞ | = | ስኑይ |
| ማክሰኞ | = | ስሉስ |
| ሮብ | = | ረቡዕ |
| ሐሙስ | = | ሐሙስ |
| አርብ | = | አርብ |
| ቅዳሜ | = | ቀዳሚት |
| እሁድ | = | እሁድ |

| የነጠላና ብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም | | |
|---|---|---|
| በአማርኛ | | በግዕዝ |
| እኔ | = | አነ |
| አንተ | = | አንተ |
| አንቺ | = | አንቲ |
| እሱ | = | ውእቱ፣ ዝንቱ |
| እሷ | = | ይእቲ፣ ዛቲ |
| እኛ | = | ንህነ |
| እናንተ | = | ለተባዕት ጾታ - አንትሙ<br>ለአንስታይ ጾታ- አንትን |
| እነርሱ | = | ለተባዕት ጾታ - እሙንቱ<br>ለአንስታይ ጾታ - እናንቱ |

# የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል

# አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

# የተማሪ መጽሐፍ

# 4ኛ ክፍል